# ፍቅርና ሰላም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ

A Monthly Amharic/English Newspaper Published by the Catholic Bishop's Conference of Ethiopia (CBCE) General Secretariat/ECS

# LINK

04 ወራት ቀረው

ካቶሊካዊ ሲኖዶስ 2014 2016

ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ኅብረት / ተሳትፎ / ተልእኮ

ቁጥር 564 | ሚያዚያ 2016 ዓ.ም | ዋጋው የኢት. 15.00 ብር


## « በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል... እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን»

## ኢሳ. 53፡ 4-5



## ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት የ2016 ዓ.ም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤ በዓል በማስመልከት ለመላው ምዕመናን ያስተላለፉት መልዕክት

ገፅ 3

## የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የአስር ዓመት ዕቅድ የመጀመሪያው ሶስት ዓመት የትግበራ ሂደት ዕቅድ አጸደቀ

ገፅ 4

የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የ25ተኛ የጵጵስና የብሩራዊ ኢዮቤልዩ ዓመትን በማስመልከት ሥጦታ ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ የቁሳዊ ሥጦታ ቀርቶ የትምህርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወጣቶች እንደሚውል በማሰብ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የሚል የገንዘብ ድጋፍ ዕድል መመቻቸቱን ገልጸው በተዘጋጀው የባንክ አካውንት መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ለዚህ በጎ አድራጎት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

### Cardinal Berhaneyesus Fund

Account Name: **Cardinal Berhaneyesus Fund**
Account Number: **1000523294338**
Commercial Bank of Ethiopia, Mahatema Gandhi Branch
Swift Code: **CBETETAA**

# ፍቅርና ሰላም

መስከረም 1967 ዓ. ም. ተጀመረ

አሳታሚ ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ



| | |
|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | አባ አበራ ማኬቦ |
| ምክትል ዋና አዘጋጅ | አቤል ሙሴ |
| ማኔጂንግ ኤዲተር | ቤዛዊት አሰፋ |
| ተቀዳሚ ረዳት አዘጋጅና ሪፖርተር/ኤዲተር | ገብሩ ሃ/ዮሐንስ |
| ምክትል ረዳት አዘጋጅ | መሳይ ማሪዮ |

| | |
|---|---|
| ፕሩፍ ሪደር | የምሥራች አሰፋ |
| ሌይ አውት 1 | ጨረቃ ዘውዴ |
| ሌይ አውት 2 | ቤተልሔም ታደሰ |
| ስርጭት | ማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ |


ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org Website - https//www.cbce-gs.org

# ርዕሰ አንቀጽ

# ድንጋዩን ከመቃብር ላይ ማን ያንከባልልናል?



በቅዱሱ ወንጌላችን ታሪክ ላይ የጌታችን የመድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መቃብር የጎበኙት ሴቶች በሚገልጸው ክፍል ``በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ጎህ ሲቀድ (ዮሐ. 20፡-1) ብሎ ይጀምራል። በአይሁድ ባህልና ወግ እንዲሁም ሥርዓት በሰልስቱ ዕለት ወደ መቃብር መሄድ የተለመደ ነው። በእኛም ባህል ሰልስት ትልቅ ቦታ አለው። ሴቶቹ ቦታው ሲደርሱ ግን ሐዘናቸውን ይበልጥ የሚጨምርና የሚያስፈራ ሁኔታ ተመልከቱ። እነርሱ ያሳሰባቸው ሌላ የጠበቃቸው ሌላ ሆነ። ቢሆንም ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚያውቁት ግንዛቤ እንዳልነበራቸው ሁኔታቸው ይገልጻል።

**በሞት ላይ የሕይወት ድል**

ሴቶቹ ክርስቶስ የተቀበረበት መቃብር በትልቅ ድንጋይ የታሸገ መሆኑን እያስታወሱ **"ድንጋዩን ከመቃብር ላይ ማን ያነሳልናል ?"** የሚለው ጥያቄ ነበር በዋናናት ያሳሰባቸው። በልባቸው ውስጥ ይህን ጥያቄ የተሸከሙት እነዚሁ ሴቶች ቦታው ሲደርሱ ይሆናል ብለው ያላሰቡት ሁኔታ ገጠማቸው። ጠባቂ ወታደሮች አልነበሩም፤ ቀና ብለው ሲመለከቱ ያ ከባድ ድንጋይ ቀድሞውንም ወደ ኋላ ተንከባሎ ጠበቃቸው። ያሰቡትን ከመፈጸም ይልቅ በደመ ነፍስ የሆነውን ነገር ለመንገር ሐዋርያት ወደ ተሰበሰቡበት ቤት በፍጥነት ተመለሱ ይሉናል ወንጌላውያን። ሐዋርያትም ከፍራታቸው ብዙ ባይወጡም የሴቶቹን ቃል በመስማት ብቻ ምንም ሳያረጋግጡ በፍጥነት ጴጥሮስና ዮሐንስ ቦታው ሲደርሱ ክርስቶስ የነገራቸውን ሁሉ በማስተዋል ወደ እዝነ ልቦናቸው ተመለሱ።

እነዚህ የመጀመሪያ ምስክሮች የእግዚአብሔርን ኃይል ሲገለጥ አዩ፣ በሞት ላይ ያለው የሕይወት ድል፤ በጨለማ ላይ የብርሃን ድል፣ በውድቀት ፍርስራሾች መካከል የተስፋ ዳግም መወለድ ስሜት እና ኃይል ለመገንዘብ ቻሉ። ሴቶቹ በወታደሮች መጠበቁ ላያውቁ ይችላሉ ነገር ግን መቃብሩ የተዘጋበት ድንጋይ ያሳስባቸዎል፤ እጅግ በጣም ከባድ እንቅፋት ነበር ለእነርሱ። የተዘጋበት ድንጋይ ሴቶቹ በልባቸው ውስጥ የሚሰማቸውን ነገር ያመለክታል። የተስፋቸውን ፍጻሜ ይወክላል። በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን የመቃብር ድንጋዮች የሚወክል ተምሳሌት ነው ።

ዛሬም ቢሆን ከባድ ድንጋዮች፣ የሰው ልጆችን ተስፋ ገድበዋል በተለይም **"የጦርነት ድንጋዮች፣ የሰብዓዊ ቀውሶች፣ የሰብአዊ መብት ረገጣ፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የተፈጠሮ ውድመት.... ከሌሎች ድንጋዮች መካከልም እንዲሁ የራሳችን ኃጢአቶች** ይገኙባቸዋል።

**ፋሲካችን የሆነውን ኢየሱስን እንመልከተው**

የሰው ዘር ሁሉ ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመለከቱት ቤተክርስቲያን ዛሬም ትጋብዛለች። ኢየሱስ በልባችን እንዲኖር ከፈቀድንለት፣ ምንም ዓይነት የውድቀት ወይም የሐዘን ልምድ፣ ምንም ያህል ስቃይ መከራ ቢሆንም፣ የእኛ የሕይወታችን ዕጣ ፈንታ ሁሌም ጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲሆንልን ጥረታችን መቀጠል አለበት።

በትንሣኤው ጌታ እንድንነሳ ከፈቀድን ምንም መሰናክል፣ መከራ ወይም ሞት ወደ ሕይወት ሙላት የምናደርገውን ዕድገት ሊያቆመው አይችልም። የእኛ ፋሲካ፣ የሕይወት አምላክ የሆነውን ጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳን ደህና መጣህ በማለት እኛ እሱን "አዎ" በማለት፣ ምንም ድንጋይ የልባችንን መንገድ አይዘጋውም፣ የትኛውም መቃብር የልባችንን ደስታ አይገድበውም።

በትንሣኤው ጌታ ዓይኖቻችንን ወደ እርሱ እናንሳ፣ እናም ከከሸፈው ተስፋችንና ሞታችን ጀርባ፣ እርሱ የሚያመጣው የዘላለም ሕይወት አሁንም እንዳለ በእርግጠኝነት ወደፊት እንቀጥል። በትንሣኤ ያገኘነው ብርሃን የልግስና እና የእውነተኛ ፍቅር ግፊቶቻችንን በሚያደናቅፉ የበለጠ ፍትሃዊ እና ሰብአዊ ከተሞችን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ወደ ኋላ በሚከለክለው የራስ ወዳድነት እና ግዴለሽነት ግድግዳዎች ውስጥ እና ማህበረሰቦች፣ በጭካኔ ጥላቻ እና በጦርነት ጭካኔ ለተደመሰሰው ሰላም ያለንን ምኞት ሁሉ የሚያሳይ ነው።

**ከኢየሱስ መቃብር ሁሉም ነገር በአዲስ መልክ ይጀምራል**

እንደ ሴቶቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ፣ "እርስ በእርሳችን እንጠይቃለን፡- ድንጋዩን ከመቃብሩ ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል? ይህ የዚያ ትንሣኤ ጠዋት አስደናቂው ግኝት፣ ግዙፉ ድንጋይ ተንከባሎ ነበር፣ የሴቶቹ ፍርሀትና መገረም የእኛም መደነቅ ነው። የጌታችን መድኃኒታችን **ኢየሱስ መቃብር ክፍት እና ባዶ ነው።** ከዚህ በመነሳት ሁሉም ነገር በአዲስ መልክ ይጀምራል። ከዚህም በላይ ከእግዚአብሔር ብቻ በቀር ማንኛችንም ልንሆን የማንችለውን መንገድ በባዶ መቃብር በኩል አዲስ መንገድ እንደሚመራ አጥብቆ አሳይቶናል። ጌታ በሞት መካከል የሕይወትን መንገድ ይከፍታል፣ በጦርነት መካከል ሰላምን፣ በጥላቻ መካከል እርቅን እና በጠላት መካከል ወንድማማችነትን ይከፍታል ።

***ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እርቅና ሰላም መንገድ***

ወንድሞች እና እህቶች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነስቷል። የሕይወትን መንገድ የሚዘጉ ድንጋዮችን የማንከባለል ኃይል ያለው እርሱ ብቻ ነው። የኃጢአት ይቅርታ ካልተገኘልን የጭፍን ጥላቻን፣ የእርስ በርስ መገዳደልን፣ ሁልጊዜ ትክክል ነን ብለን እና ሌሎችም ተሳስተናል የሚለውን ግምት ለማሸነፍ የሚያስችል መንገድ የለም። የኃጢአታችን ሥርየትን በመስጠቱ ለታደሰ ዓለም መንገድ የሚከፍተው ክርስቶስ ብቻ ነው። በሌሎች የአለም ክፍሎች በዓመፅ፣ በግጭት፣ በምግብ እጦት እና በአየር ንብረት ለውጥ ውጤቶች ለሚሰቃዩ ሁሉ ክርስቶስ ከሞት የተነሳው የተስፋ መንገድ እንዲከፍትላቸው በጸሎታችን እንርሳቸው።

በዘመናችን በልጁ ትንሣኤ የተሰጠንን ህይወት በምናከብርበት ቀን ለእያንዳንዳችን ያለውን ወሰን የሌለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር እናስብ። እንዲሁም የሕይወት ውድ ስጦታ ምን ያህል የተናቀ ነው! ስንት ልጆች እንኳን ሊወለዱ አልቻሉም ? ስንቶቹ በረሃብ ሞተው አስፈላጊ እንክብካቤ ተነፍገው ወይም የጥቃት እና የጥቃት ሰለባዎች ናቸው? ስንት ሕይወት አለ? በሰዎች ውስጥ እየጨመረ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ምላሽ እየተሰጠ ነው?። ክርስቶስ ከሞት ባርነት ነፃ ባወጣን ቀን እኛም ያገኘነውን ጸጋ አናቆሽሸው።

በማጠቃለያ በኢትዮጵያ የምትገኘው ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን መንፈሳዊና ባህላዊ ሥርዓት አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በሰልስት ዕለት ቤተክርስቲያን ተገኝቶ በሞት ለተለየው/ችው ወገናችን በጸሎት ማሰብ ምን ያህል በክርስቶስ ትንሣኤን ያገኘነው ተስፋ እና እምነት ለቀሪው ሕይወታችን ስንቅ ይሁነን። እኛም በጸሎታችን በልጅህ በክርስቶስ ትንሣኤ ዓለምን ያዳንህና ያዳስህ አምላክ ሆይ በእናቱ በድንግል ማርያም አማላጅነት መጨረሻ ደስታ እንድናገኝ ፈቃድህ ይሆንልን ዘንድ በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንለምን ማለትን እንርሳ።

***መምህራችን ሆይ ለመስቀልህ እንሰግዳለን***
***ቅድስት ትንሣኤህንም ሁላችን አሁንም ለወትሮም እናከብራለን።***

## የፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ኤዲቶሪያል ቦርድ

※※※

**ለመላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፈቃድ ያላቸው ወገኖች ሁሉ እንኳን ለ2016ዓ.ም የትንሣኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ**

※※※

**በማለት ምኞቱን ይገልጻል። እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያን ይባርክ!!!**

## የሲኖዶሳዊ ጉዞ ጸሎት

*መንፈስ ቅዱስ ሆይ! ና!*
*እነሆ በስምህ ተሰብስበን በፊትህ ቆመናል ወደ እኛ ተመልከት፤ እርዳንም። ብቸኛ መሪያችን አንተ ነህ ልቦቻችንን ከፍተህ ማደርያህ አድርግልን። ማድረግ ያለብንን ሁሉ አንተ አስተምረን፣ ሁላችንም በአንድ ላይ መከተል ያለብንን መንገድ አንተ አሳየን። እኛ ደካሞች እና ኃጢአተኞች ነንና፤ ሁከት እንዳናስፋፋ፣ አላዋቂነት ወደ ተሳሳተ ጎዳና እንዳይመራን፣ አድልዎ በድርጊቶቻችን ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድርብን እርዳን። ከእውነት መንገድ እንዳንስት፣ ወደ ዘለዓለማዊ እና ትክክል ወደሆነው ሕይወት አብረን እንጓዝ ዘንድ ከአንተ ብቻ የሆነውን የሕብረት መንፈስን ስጠን።*
*ይህን ሁሉ በሁሉም ቦታ እና በሁሉም ሰዓት ከአብ እና ከወልድ ጋር አብረህ በሥራ ላይ የምትኖርን አንተን እንለምንሃለን፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አሜን።*

## የዕርቀ ሰላም ጸሎት

ፈጣሪ ሆይ የሰላም መሳሪያ
እንድንሆን አድርገን።
ጥላቻ ባለበት ፍቅር፤
በደል ባለበት ይቅርታ፤
ክርክር ባለበት ስምምነት፤
ጥርጣሬ ባለበት መተማመን፤
ሐዘን ባለበት ደስታ፤
ጨለማ ባለበት ብርሃን፤
እንዲገኝ እናደርግ ዘንድ አብቃን።
ፈጣሪ ሆይ፤ በሕዝባችን መካከል ዕርቅ ይውረድ፤ ሰላምህ ይስፈን፤ አገራችን ኢትዮጵያን ባርክልን ጠብቅልን።
አሜን!

## ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት

# የ2016 ዓ.ም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤ በዓል በማስመልከት ለመላው ምዕመናን ያስተላለፉት መልዕክት

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።**

## ‹‹እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ›› ዮሐ 11፤25

**ብፁዓን ጳጳሳት**
**ክቡራን ካህናት፤ ገዳማውያንና/ውያት**
**በጎ ፈቃድ ላላቸው ሰዎች**
**በክርስቶስ የተወደዳችሁ**
**የእግዚአብሔር ሕዝቦችና ምዕመናን**
**በተለያየ ምክንያትና ሁኔታ**
**ከአገራችሁ ውጪ የምትገኙና**
**የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ**
**ኢትዮጵያውያን ምዕመናን በሙሉ**



እንኳን ለ2016 ዓ.ም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል አደረሳችሁ በማለት በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንና በእራሴ ስም መልካም ምኞቴን አቀርብላችኋለሁ።

ከሁሉ በፊት የትንሣኤን ምሥጢር ለማስተዋል የመስቀሉን ምሥጢር መመርመር ያስፈልጋል፣ የመስቀሉ መከራና የትንሣኤው ብርሃን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ለመሆኑ የክብር ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ለምን ወደዚህ ስቃይ መጣ? ብዙ ሰዎች የሚጠቅማቸውን ነገር ያገኙ ዘንድ በመከራ ያልፋሉ ዞሮ ዞሮ በመጨረሻ ‹‹የእኔነትን›› ፍላጎት ለማርካት ብዙ መሯሯጥ ብዙ መቸገር ሊከሰት ይችላል። እንዲህም ሆኖ የተፈለገውን ነገር በተቻለ መጠን ብዙ ሳይለፋ ለማግኘት መጣርም በብዙዎች ዘንድ የሚታይ ነገር ነው።

የኢየሱስ ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ ነው፣ እሱ ስለሰዎች ደኅንነትና ስለሰዎች ፍቅር ራሱን አሳልፎ ሰጠ። በእርግጥም ገና ኢየሩሳሌም ሳይገባ በገሊላ ክፍለ ሀገር ሲያስተምር ሊገድሉት ሲሞክሩ በመሀከላቸው እንዳለፈ በወንጌል ተጽፎአል። ሥልጣን እንዳለውና በራሱ ፍቃድ ካልሆነ በቀር ማንም ጉዳት ሊያደርስበት እንማይችል እንረዳለን (ዮሐ 18፤21)፤ ይህን የኢየሱስን የመከራ ምሥጢር ከብዙ አቅጣጫ ልንመለከተው እንችላለን። ስለሌሎች በገዛ ፍቃዱ ተሰቃይቶ ሞተ።

ተደጋግሞ እንደሚያጋጥመውም የኢየሱስ መልካም ሥራ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ ቅናትን አሳደረ። በመልካም ሥራው ከእርሱ ጋር ከመተባበር ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግስት መስፋፋት ተቃረኑ። ሰው በቅናት ተነሣሥቶ ንፁሁን ሰው ማጥፋት እንዳለ ሁሉ ኢየሱስንም ለመግደል ተማከሩ። ለተገለሉት ለተቅበዘበዙትና የእግዚአብሔር ጽድቅ ለጠማቸው ምሕረትን ማምጣቱ አላስደሰታቸውም። የሰበከው አዲሱ የፍቅር ህግ አልጣማቸውም፤ ውስጣቸው ስለተረበሸና ቅናቱ ጥላቻን በመውለዱ እስከ መስቀል ሞት ውሳኔ ደረሱ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለው መከራ በሱ ዘመን ለነበሩት ብቻ ሳይሆን ከሱ በፊትና በኋላ ለሚመጡትም በሙሉ ትሩፋትን ያስገኛል። ንፁህ የአምላክ ልጅ ደም ኃጢአታችንን ያጥባል። የቀድሞው አዳም በትዕቢት እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ተንጠራርቶ ውድቀትን አመጣ። ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ በትህትና ክብርንና ትንሣኤን አመጣ (ሮሜ 5፤ፊሊ፣2)

ለኛ ለክርስቲያኖች ትልቁ ምስጢራችን የትንሣኤ የምሥራች ነው። የሰው ልጅ ሕይወት በሞት የሚደመደም እንዳልሆነ እነሆ የክርስቶስ መነሣት ያስተምረናል። የጥምቀታችንም ምሥጢር ይህ እንዳልሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ለኃጢአት ከክርስቶስ ጋር ሞቶ ለአዲስ ሕይወት ከክርስቶስ ጋር መነሣትን ያስተምረናል (ሮሜ 6)። እንግዲህ የክርስቶስ ትንሣኤ ሰውን ብቻ ሳይሆን ፍጥረትን በሙሉ ያድሳል። ዓለም በሙሉ ለፈጠራትና ለሚያድሳት ጌታ ምስጋና እልል ትላለች። እኛም በዚህችው ዓለም እንገኛለንና አብረን ምስጋና፤ ውዳሴ፤ ስግደትና አምልኮ፤ ዝማሬና እልልታ ድል ለነሣው ክርስቶስ እናቅርብለት።

ከመስቀል በኋላ ትንሣኤ ባይኖር ኖሮ የክርስትና ሃይማኖትም ባልኖረ ነበር። ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ ያከናወነው ጉዞ መጨረሻው የሚያሳዝን ታሪክ ሆኖ በቀረ ነበር። ክፋትም ድል ነሣ፤ በጎ ነገር ተሸነፈ በተባለ ነበር። የሰው ልጆችም ተስፋ በጨለመ ነበር። ነገር ግን ትንሣኤ ልዩ ያልተጠበቀ ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነውን መጨረሻ ድል ያበሥራል። የክርስቶስ ሞት ሞትን ደመሰሰ። የክፋት መሸነፍና የሰይጣን ማፈር ሆነ። ኀዘን በደስታ ተለወጠ። እውነተኛው የዓለም ብርሃን የሕይወትንና የትንሣኤውን ብርሃን ገለጠ።

ትንሣኤ ደቀመዛሙርቱን ከሞትና ከጥርጣሬ ዓለም አወጣቸው። ኢየሱስን የሚወደው ደቀመዝሙር ያመነው የመቃብሩን ባዶ መሆን በማየት ነው። በኢየሱስ ደረት ላይ ተደግፎ የሰማውን ቃል በልቡ ይይዘው እንደነበር መገመት ይቻላል። ምንም ሳይፈራ በመስቀል ሥር የተገኘውም የእግዚአብሔር ልጅ ፍቅር በልቡ ታትሞ ስለነበር ነው። በመስቀል በኩል አልፎ ወደ ትንሣኤ ምስጢር ደጃፍ ደረሰ። መቅደላዊት ማርያምም ‹‹ለምን ታለቅሻለሽ›› ላላት ጌታ የምታለቅስበትን ምክንያትም ከነገረችው በኋላም የኢየሱስን ሥጋ ወደሌላ ቦታ ወስዶት ይሆን ብላ በማሰብ ያደረገበትን እንዲነግራት ዘበኛው መስሏት ጠየቀችው። ይህ ምንኛ ታላቅ እምነትና ፍቅር ይሆን? የጌታን አስከሬን ማግኘት አለብኝ በማለት ነበር የምትፈልገው። እሷ ግን ከአስከሬን የበለጠ ልታገኝ ነው። ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን በመጀመሪያ አላወቀችውም ነበር። በስሟ ሲጠራት ነው ያወቀችው፤ እርሱ በጎቹን በየስማቸው ይጠራቸዋልና። እርሷም ከእንግዲህ ትንሣኤውንና እርገቱን ማብሠር ነው የሚጠበቅባት። ከመስቀሉ በፊት ባለው ዓይነት እርሱን ልትይዘውና ልትመለከተው አያስፈልግም፣ እርሱ ወደ አባቱ ወደ አብ እየተጓዘ ነውና።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ሲነሣ ለሐዋርያቱ ያቀረበላቸው ሰላምታ ‹‹ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን›› (ማቴ 20፤19) የሚለው ሰላምታ ነበር። ይህም መስቀል የሰላም ምንጭ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። እንዲሁም መስቀል ስለ እግዚአብሔር ማንነት፤ ስለ ሰው ልጅ ሕይወት እና ስለ ፍጥረታት እውነቱን የሚያስተምር የእውነትም ምንጭ ነው። የመስቀሉ ሰላም ከላይ የተጠቀሱት እሴቶች በሙሉ ያካትታል። የሕይወትን ክቡርነት፤ ፍቅርን፤ የአገልጋይነትን መንፈስን፤ ልግስናን፤ ፍትሕን፤ ምሕረትን፤ ሥራንና እረፍትን ይመለከታል። እነሆ የዓለም ንጉሥ ተነሥቷልና እንቀበለው፣ እናክብረው፣ እናመስግነው፣ ሁላችንም በትንሣኤው ብርሃን ለአገራችንና ለሕዝባችን የሰላም መሣሪያዎች እንሁን። የችግሮቻችን መውጫ ቁልፍ ሰላም ብቻ ነው። ለሰላም እንጸልይ እንትጋ። ሰላምንንና ፍቅርን ጌታ በትንሣኤው ያድለን።

**የተወደዳችሁ ምዕመናን**

ይህን ትልቅ በዓል ስናከብር የተቸገሩትን፤ የተሰደዱትን፤ የተፈናቀሉትንና የተራቡትን፤ በግጭቶች ዙሪያ የሚገኙትን በማሰብና በመርዳት ፋሲካችንን በጋር እንድናከብር አደራ ማለት እወዳለሁ።

በመጨረሻም በዚህ የትንሣኤ በዓላችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለታመሙት ምሕረትን፤ ላዘኑት መጽናናትን፤ በየማረሚያ ቤቶች ለሚገኙት መፈታትን፤ በችግርና በመከራ ላይ ለሚገኙት ብርታትን ለአገራችንና ለሕዝባችን ሰላምን ይስጥልን።

የትንሣኤ ባለቤት የሆነው ጌታ ሰላምን ያውርድልን፣ ይባርከን፣ ይቀድሰን !

† ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ
ሊቀጳጳሳት ዘካቶለካውያን
የኢትዮጵያ ካቶሊካት ቤተክርስቲያን
ጳጳሳት ጉባዔ ፕሬዘዳንት

## የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት...

ከገፅ 1 የዞረ

ከሚያዝያ 8 - 11 ቀን 2016 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ላለፉት ሁለት ዓመታት ተዘጋጅቶ የቀረበውን የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የአስር ዓመት ዕቅድ የመጀመሪያው የሶስት ዓመት የአፈጻጸም ሂደትን በይፋ ለማስጀመር በቅዱስ ፍራንቼስኮስ የነገረ መለኮት ተቋም አዳራሽ ውይይት አደረገ። ጉባኤው በብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ መሪነት ብፁዓን ጳጳሳት፣ ክቡራን ገዳማውያን እና ገዳማውያት፣ ክቡራን አባቶች፣ ከሀገረስብከት የተወከሉ የጳጳሳት እንደራሴዎች፣ የሐዋርያዊ ሥራ አስተባባሪዎች፣ የልማት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የጠቅላይ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች፣ የምዕመናን እና የወጣት ተወካዮች፣ የአጋር ድርጅት ተወካዮች እና ባለሙያዎች በተገኙበት ሲካሄድ ቆይቷል።

ይህ መርሃግብር በቤተክርስቲያን ቀኖናዊ መዋቅር አስተዳደር፣ በሐዋርያዊ ዘርፍ፣ በልማት ዘርፍ፣ በአስተዳደር ዘርፍ፣ እንዲሁም በሁሉም ዘርፎች ላይ በመካተት የቤተክርስቲያን ጥበቃና ከለላ የሚያረጋግጡ፣ በቂ የክትትል ሂደት የሚተገብሩ መሆናቸውን፣ ሁሉንም የቤተክርስቲያን አካላትን የሚያካትት በተለይም ሴቶችን የሚያበቃ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን ለማረጋገጥ የተዘጋጀ የምክክር መድረክ መሆኑ ተገልጿል።

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ የእምድብር ሀገረስብከት ተተኪ ጳጳስ እና የጠቅላይ ጽ/ቤት ጠቅላይ ጸሐፊ በመጀመሪያው መርሀግብር የቤተክርስቲያን አወቃቀር ከካቶሊካዊት ቤተክርስትያን ቀኖና በመመስረት ለማጠናከር ሊተገበሩ የሚገቡ ዝርዝር ዕቅዶችን በጉባኤው ያቀረቡ ሲሆን በመቀጠልም በየዘርፉ የሚገኙ የዘርፍ መሪዎች የሶስት ዓመት ዕቅዶቻቸውን አቅርበዋል። በሁሉም የአገልግሎት ዘርፎች የቀረበው ግብዓት እና ዕቅድ ላይ ተሳታፊዎች ሀሳቦችን ሰጥተዋል። በመጨረሻም ጉባኤው በሁሉም የቤተክርስቲያን አገልግሎት ዘርፎች ላይ የታቀዱትን ተግባራት ዘርፎቹን በሚመሩት አካላት በማቅረብ ገምግሞ አፅድቋል።

በጉባኤው የጸደቁት ተግባራት በመጀመሪያ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛው የትግበራ አመታት በቅደም ተከተል በጠቅላይ ጽ/ቤት፣ በሀገረስብከት፣ በገዳማት፣ በቁምስናዎች እንዲሁም በሁሉም የካቶሊክ የጤና እና የትምህርት ተቋማት በየደረጃው የሚተገበሩ ይሆናል። ለዚህም ታላቅ የቤተክርስቲያን አቅጣጫ የሁሉም የቤተክርስቲያን አካላት በተለይም የብፁዓን ጳጳሳት እና የምዕመናን ባለቤትነት እንዲጎላ ከተሳታፊዎች ጥሪ ቀርቧል።

በጉባኤው ማጠናቀቂያም የአስር ዓመት ዕቅዱ አማካሪ የሆኑት አቶ ስኮት በቀጣይ የሚደረጉ ሂደቶችን ለተሳታፊዎች ያቀረቡ ሲሆን በጉባኤው በተገኙት ብፁዓን ጳጳሳት፣ የጳጳሳት እንደራሴዎች፣ የገዳማት ተወካዮች፣ የምዕመናን እና የወጣት ተወካዮች፣ አጋር ድርጅቶች፣ የጠቅላይ ጽ/ቤት እና የሀገረስብከት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ባለቤትነት ወደተግባር ለማውረድ ቁርጠኝነት ተወስዷል።

ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን በጉባኤው ማጠናቀቂያ ባስተላለፉት መልዕክት ይህ ሂደት በሲኖዶሳዊ መንገድ በመንፈስ ቅዱስ የተመራ መሆኑን አስታውሰው በዚህ ጉባኤ በአካል ባይገኙም በሀሳብ እና በጸሎት እንዲሁም ተወካዮቻቸውን በመላክ አብሮነታቸውን የሳዩ ብፁዓን ጳጳሳትን በተለይም ብፁዕ አቡነ ተስፋስላሴ የአዲግራት ሀገረስብከት ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ጸጋዬ የቀድሞ የሶዶ ሀገረስብከት ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ሮቤርቶ የጋምቤላ ሀገረስብከት ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ አንጀሎ የሮቤ ሀገረስብከት ጳጳስ፣ ብፁዕ አባ አንጀሎ አንቶሊኒ የሮቤ ሀገረስብከት ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ አንጀሎ ፓጋኖ የሀረር ሀገረስብከት ጳጳስ ለትግበራው ድጋፍ አብሮነታቸውን ገልጸዋል።

ብፁዕ ካርዲናል በመቀጠል "ምዕመናን የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አንዱ ክፍተት የሆነውን የጳጳሳት ቁጥር ማነስ በተለይም በሐዋሳ ሀገረስብከት እና በነቀምቴ ሀገረስብከት ጳጳሳት እንድናገኝ እኛ እየጸለይን ነው ምዕመናንም እንድታግዙን" ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ብፁዕ አባታችን የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ከኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና ከወንጌላውያን ህብረት ጋር በመተባበር በሀገራችን ከፍተኛ የሰብዓዊ ድጋፍ የሚያፈልጋቸው ቦታዎች ላይ ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ መልኩ ለመድረስ እና የሁሉም ድምጽ ለመሆን ጥረት በማድረግ ላይ መሆኗን ገልጸው ለዚህም የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ልሳን የሆኑትን የፍቅር እና ሰላም ጋዜጣ እና የሰላም ካቶሊክ ቴሌቭዥንን በመደገፍ የስብከተ ወንጌል፣ የፍትህ እና የሰላም ድምፅ መሆን እና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ለምድራችን ጨው እና ብርሃን መሆን እንደሚገባን ገልፀዋል። በመጨረሻም ብፁዕ ካርዲናል በዚህ ሂደት ያገዙትን የጠቅላይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች፣ የሰበካ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች፣ የገዳማት ኃላፊዎች እና የአጋር ድርጅቶች አመስግነዋል።

ብፁዕ አቡነ ሉቃስ የእምድብር ሀገረስብከት ተተኪ ጳጳስ እና የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ጠቅላይ ጸሐፊ በማጠቃለያ መልዕክታቸው "ሙሴ የተስፋይቱን ምድር እያያት ሳይደርስ እንደቀረው እኛም ልናያት የምንሻትን ቤተክርስቲያን ሳናያት እንዳንቀር ሁላችንም የበኩላችንን እንድንወጣ እና በሲኖዶሳዊ መንገድ በየዘርፉ ያለን አመራሮች ሰራተኞቻችንን ምዕመናንን እንድንመራ አደራ እላለው" ብለዋል። በመጨረሻም ይህንን የዕቅድ እና የትግበራ ሂደት በማማከር እና በማሳለጥ ሲያስተባብሩ የቆዩትን አቶ ስኮት ሌፌቨሬ ከጠቅላይ ጽ/ቤቱ ጋር ያላቸውን አገልግሎት ጊዜ በማጠናቀቃቸው ጉባኤው በታላቅ ምስጋና ሸኝቷቸዋል።





# ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ተካሄደ

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ማለትም ከአፍሪካ የሃይማኖት ተቋማት ሕብረት (United Religions Initiative 'URI' for Africa) እና ከቡድን 20 የሃይማኖቶች ሕብረት ፎረም (G-20 Inter Faith Forum Association)፣ ከአፍሪካ ሕብረት የዜጎች እና ዲያስፖራ ዳይሬክቶሬት እና ከአፍሪካን ሕብረት የሃይማኖቶች ውይይት ፎረም ጋር በመተባበር በክብርት የኢፌዲሪ መንግስት ፕረዚዳንት የበላይ ጠባቂነት የተዘጋጀው ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ "የእምነት ተቋማት ትብብር ለሰላም፣ ለሰብዓዊ ክብር፣ ልማትን እና የአካባቢ ጥበቃን ለማጠናከር እንዲሁም የጥላቻ ንግግርን፣ ግጭትን እና ብሄርተኝነትን ለመቃወም" በሚል መሪ ቃል ለሁለት ቀናት የሚቆይ ጉባኤ አዲስ አበባ በሚገኘው ሂልተን ሆቴል ከሚያዚያ 7 እስከ 8 ቀን 2016 ዓ.ም. ተካሂዷል።

በዚህም ጉባኤ ላይ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካዊያን የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ፕረዚዳንትን ጨምሮ ክቡር ዶክተር ኬይረዲን ተዘራ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሰላም ሚንስተር ሚኒስትር ድኤታ፣ አምባሳደር ሙሴ ሃይሉ የአፍሪካ ሕብረት የሃይማኖት ተቋማት ኢኒሺዬቲቭ የአፍሪካ ቀጠና ዳይሬክተር እና የአፍሪካ ሕብረት የተባበሩት መንግስታት ተጠሪ፣ የተለያዩ ሃይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ ከተለያዩ ክፍለ ዓለማት የመጡ ተሳታፊዎች፣ የተከበሩ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ጉባኤ የበላይ ጠባቂ አባቶች፣ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ዲፕሎማቶች፣ የየሀገራት ተወካዮች፣ የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ተወካዮች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል።

በጉባኤው ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ "የሃይማኖት ወይም የእምነት ተቋማት ትብብር ለሰላም፣ ለሰብአዊ ክብርን፣ ልማትን አከባቢ ጥበቃን ለማጠናከር እና የጥላቻ ንግግርን፣ ግጭትን እና ጠባብ ብሄርተኝነትን ወይንም ትምክህተኝነትን ለመቃወም" በሚል መሪ ቃል የሚከናወነው ይሄ ሁለተኛው ዓለም አቀፍ ጉባኤ በየካቲት ወር የመጀመሪያ ሳምንት የሚታሰበው የዓለም ሃይማኖቶች ትብብር ሳምንት እና በየዓመቱ ሚያዚያ 5 ታስቦ የሚውለውን የዓለም አቀፉን የወርቃማ ህግ ቀንን ታሳቢ በማድረግ የዓለም ሃይማኖቶች ትብብር እና ቅንጅት ለማጠናከር ታስቦ የተዘጋጀ ጉባኤ ነው ብለዋል።

ጉባኤው ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ባለፈው ዓመት የተዘጋጀው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የምክክር ጉባኤ በዋናነት ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ በሆኑ ጉዳዮች፥ በተለይም በሰላም፣ በሰብአዊ ክብር፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በዘላቂ ልማት፣ እና በሃይማኖት ወይም በእምነት ነፃነት ላይ ትኩረቱን አድርጎ ተካሂዶ እንደነበር ይታወሳል።

የመጀመሪያው ጉባኤ ከያዛቸው ዓላማዎች አንዱ፣ የአፍሪካ ሕብረት 55 አባል ሀገራቱን በመወከል የG20 አባል እንዲሆን ምክረ ሃሳብ የቀረበበት እና ሃሳቡን ሌሎች አጋሮች እና የሀገራት መሪዎች ጭምር ድጋፍ በማግኘቱ መስከረም 2023 በሀገረ ህንድ፣ በኒውደልሂ ከተማ በተካሄደው የቡድን 20 አባል ሀገራት የመሪዎች መደበኛ ስብሰባ ላይ ምክረ ሃሳቡ ተቀባይነት አግኝቶ፥ ህብረቱ የቡድን 20 ቋሚ አባል እንዲሆን መወሰኑ ይታወሳል።

ይህም ጉባኤው በሀገራችን ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይወሰን፥ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ጭምር አዎንታዊ ሚናውን ለመወጣት አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ጥረት እያደረገ ለመሆኑ አንዱ ማሳያ ነው።

ዓለም አቀፍ ጉባኤው በዋናነት በሁሉም ሃይማኖቶች አስተምህሮ ጠንካራ መሰረት ያለው የሰላም እና የአብሮነት የመከበር እሴትን እንዲሁም ዓለም አቀፍ ወርቃማ ሕግን ይበልጥ ለማስተዋወቅ እና ለማጠናከር ሃይማኖቶች ለሰላም፣ ለሰብአዊነት፣ ለአከባቢ ጥበቃ እና ለሃይማኖትና እምነት ነፃነት መጠበቅ ያላቸውን ገንቢ እና አዎንታዊ ሚናቸውን እንዲያጠናክሩ እና ከሃይማኖቶች አስተምህሮ ጋራ ለሚቃረኑ አሉታዊ አስተሳሰቦችና ሕገ ወጥ ተግባራትን በተባበረ አቅም ለመከላከል እንዲቻል ሀገራት አስፈላጊ የሆኑ የሕግ ማሻሻያዎችን እንዲያደርጉ አማራጭ ሃሳብ ይቀርባል ተብሏል።

ከዚህም በተጨማሪ የምክክር ጉባኤው ሀገሪቷ ለብሄር እና ብሄረሰቦች፣ ሃይማኖቶች እና እምነቶች ብዙሃነት የተገነባች ምድረ ቀደምት የሚለውን የቱሪዝም መገለጫ በተጨባጭ ማሳያ ለማስተዋወቅ መልካም አጋጣሚ ከማስተዋወቁም ባሻገር፥ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ የገፅታ ግንባታ እና ሀገራችን የቱሪዝም መዳረሻነቷን ለማስፋት የላቀ አስተዋጽዖ እንደሚያበርክትም ተገልጿል።

ጉባኤው ከተባባሪ አጋሮች ጋር በመሆን እንዲህ ዓይነቱን ዓለም አቀፋዊ መድረኮችን በማዘጋጀት ጠቃሚ ልምዶችን እና ተመክሮዎችን ከማግኘቱም ባለፈ የሃይማኖት ተቋማት ተልእኮዋቸው ድንበር የለሽ ከመሆኑ አንፃር ሁሉንም የሰው ልጆች እንደ አንድ ቤተሰብ በማስተሳሰር ኢ - ፍትሃዊነትን እና በደልን፣ ኃጥአትን እና ኢ-ሃይማኖታዊነትን ለመከላከልም ይረዳል የተባለ ሲሆን፥ ይህም ጉባኤው ከተቋቋመበት መሰረታዊ መርህ እና ዓላማ ጋራ በእጅጉ የሚስማማ እንደሆነ ያሳያል ተብሏል።

"የሃይማኖት ተቋማት ተልዕኳቸው ድንበር የለሽ ነው" ያሉት ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ በመጨረሻም ይህ ዓለም አቀፍ ጉባኤ በዚህ መልኩ እንዲከናወን ልዩ ልዩ ተሳትፎ እና አስተዋጽዖ ላበርከቱ ባለድርሻ አካላት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከትምህርት ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**‹‹ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው?**
**ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?››(ሚኪያስ 6፡8)**



በክቡር አባ አብነት አበበ
ዘማኅበረ ልኡካን/ ላዛሪስት

# መልካምን ለመሥራት እግዚአብሔርን መፍራት

*ሁላችንም በራሳችን መንገድ መልካም ነገርን እናደርጋለን፤ ነገር ግን የሚያነሳሳን ምክንያት ምንድን ነው ብለን ስንጠይቅ በተለምዶ ሶስት ምክንያቶችን እናገኛለን፤ እነርሱም፡ ግዴታችን/ኃላፊነታችን ስለሆነ፣ ሽልማትን ለማግኘት ወይም ቅጣትን ከመፍራትና በመጨረሻም ለፍቅር ብለን ስለምንሰራ የሚሉት ናቸው። ዝርዝሩን እንመልከት።*

**1) ግዴታ/ኃላፊነት/**

ለምሳሌ ነርሶች ሥራቸውን የሚሰሩት ራሳቸውን በመስጠት ነው፤ ለምን፤ እንደ ክርስቲያን በእሁድ ዕለት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ እናስቀድሳለን እናመለካለን ግን ለምን፤ ሰው ሲሞት ለቅሶ እንደርሳለን፤ ለምን፤ አብዛኛውን ጊዜ የምናደርጋቸውን ነገሮች የምናደርገው መደረግ ስላለበት ወይም ግዴታ ስለሆነብን ነው።

**2) ሽልማት ለማግኘት ወይም ከቅጣት ለማምለጥ**

ከልጅነታችን ጀምሮ ከተለማመድናቸው ነገሮች አንዱ ስለሚሰጠን ነገር ስንል የታዘዝነውን ነገር ማድረግን ነው፤ ለምሳሌ በትምህርታችን ጥሩ ውጤት ካመጣን ወይም በጥሩ ውጤት ካለፍን ሽልማት እንደሚሰጠን ሲነገረን ለሽልማቱ ስንል እንሰራለን፤ አትሰረቅ፤ እግዚአብሔር ሺ ዓይኖች ስላሉት ያይሃል፤ እናም ወደ ገሀነም ይከትሃል፤ ጌታ ሆይ እኛ ሁሉንም ነገር ትተን ተከተልንህ፤ ታዲያ የምናገኘው ምንድን ነው ከሚሉት አባባሎች ጀርባ ሽልማትን ፍለጋ ወይም ቅጣትን ለመሸሽ አንደምናደርግ ያሳያሉ።

**3) ፍቅር**

ለምናደርገው መልካም ሥራ ሌላው ምክንያት ፍቅር ነው። ሰዎች ሲቸገሩና የእኛን እርዳታ ሲፈልጉ ከእነርሱ ምንም ሳንጠብቅ ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ስንል የምንሰጠው አገልግሎት ነው። ስለ ፍቅር ስንል የምናደርግ ከሆነ (በውስጣችን ፍቅር ሲኖር) ፍላጎታችንና ኃይላችን/የማድረግ አቅማችን ይጎለብታል፤ በዚህ ምክንያት ለሌላው ማደግ ስንል መርዳት እንፈልጋለን ወደንና መርጠን እናደርጋለን።

ዛሬ በአገራችን ኢትዮጵያ በብዙዎቻችን ዘንድ በሚባል መልኩ የመልካም ሥራ ተካፋይ ለመሆን ሥራችንን በኃላፊነት የመወጣት ስሜት ጠፍቶ ሽልማትን መሻት ይቅርና ላጎደልነው በጎ ተግባር በፈጣሪ ፊት እንደምንጠየቅ ተዘንግቶ ከዚህም ባሻገር ስለሞያችን ወይም ስለምናገለግለው ሕዝብ ፍቅር ስንል መሥራት ጊዜው ያለፈበት እስኪመስል ድረስ ከመልካም ሥራ መራቃችን እንዲሁም በመካከላችን ያለው ጦርነትና ጠብ (ያዕ.4፡1) የስጋ ሥራ የሆኑት ‹ዝሙት፡ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ አስማት፣ ጠላትነት፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ መሶልሶል (ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ/ ልቅ የሆነ ወሲባዊ ተግባር የሚፈጸምበት ድግስ)...(ገላ. 5፡19-21) በመካከላችን ተንሰራፍቶ ስናይ ለእኩይ ተግባር አደላችሁ ያስብላል።

የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የነገረ መለኮት (የካቶሊክ ቲኦሎጂ) ሊቅ የሆነው ዶክተር እስኮት ሃን በአንድ ወቅት ሲያስተምር ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ከውስጥና ከውጭ ስላለበት ጫና የሚከተለውን ጠቅሶ ነበር፤ ይህም የዘመኑ ቤተሰብ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የዚህ ጫና ተጠቂ መሆኑን ያመለክታል።

በምንኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ (በባህላችን) ቁሳዊ ኃብትን ማፍቀር ተመለከ፤ ግብረ ገብ አልባነት ማራኪ ተደረገ፤ እውነት መነመነች፤ ኃጢአት የተለመደ (ቀላል) ነገር ሆነ፤ ትዳርን ማፍረስ (መፋታት) በምክንያታዊነት ተደገፈ፤ ጽንስ ማስወረድ ሕጋዊ ተደረገ፤ በቴሌቭዥንና (በመረጃ መረብ ትስስር እና) በፊልሞች የሚታዩ ወንጀሎች ህጋዊ ፈቃድ ተሰጣቸው፤ እጾችን (ሃሽሽ) መጠቀም ቀላል እንዲመስል ተደረገ፤ ቀልዶቻችን ከመስመር ወጡ (ቅጥ አጡ)፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ልበ ወለድ ተቆጠረ፤ ቤተክርስቲያን ተቀለደባት ፤ እግዚአብሔር ወደ ጎን ተተወ፤ ክርስቲያኖች እንደ ሰይጣን (ክፉ/መጥፎ) ተቆጠሩ፤ አረጋውያን እንደ ሰው የሚገባቸውን ክብር አጡ (ከሰው በታች ተቆጠሩ)፣ የመዳን ተስፋ የሌላቸው ሕሙማን እንዲሞቱ ተደረገ፤ ድሆች ተበደሉ፤ የአእምሮ ሕሙማን ተገለሉ፤ ልጆቻችን ፍዝዝ ድንዝዝ እንዲሉ ተደረጉ፣ በቤታችን ውስጥ ጸባያችን ስርአት አልበኝነትን አነገበ፤ ንግግራችን እኛን የማይመጥን ሆነ፤ እምነታችን ዓለማዊ መንፈስን ተላበሰ፤ ሁሉም ነገር ገንዘብ የማግኛ መንገድ ሆነ፤ እኛ ክርስቲያኖች መገኘት በሌለብን ቦታ (ሁኔታ) ውስጥ ሆነን ብዙ ጊዜ ተገኘን፤ እረኞቻችን ተስፋ ቆረጡ (ሞራላዊ ሕይወታቸው ዝቅ አለ)፤ እምነታችን ተከፋፈለ፤ ስለዚህ ክርስቲያናዊ ምስክርነታችን ተአማኒነትን አጣ። ታድያ ምን እናድርግ በማለት ይጠይቅና ምላሹን እንዲህ ሲል ያቀርባል፣ አምልኮአችንን ሕይወት እንዝራበት፤ ልዩነታችንን እናጥብበው፤ የተኙ ምእመናንን እንቀስቅሳቸው፤ ቤተሰባዊ ሕይወታችን ይታደስ፤ እንደገና ስብከተ ወንጌል ያሻናል ብሏል አሜሪካዊው ዶክተር እስኮት። እኛም ዛሬ ጥያቄአችን ከመጥፎ ሥነ ምግባራችን ተላቀን የመልካም ሥራ ተካፋዮች ለመሆን ‹‹ጌታ ሆይ፤ ምን ላድርግ?›› (ሐዋ.ሥ 22፡10) በማለት እግዚአብሔር አምላካችን ከእያንዳንዳችን ምን እንደሚፈልግ ልንጠይቅ ግድ ይለናል።

## እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?

***እርሱን እንድንፈራው፣ እንድንታዘዘው፣ እንድንወደውና እንድናገለግለው ይፈልጋል***

‹‹እሥራኤል ሆይ፤ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? አምላክህን እግዚአብሔርን እንድትፈራው፣ በመንገዶቹ ሁሉ እንድትሄድ፣ እንድትወድደው፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ እንድታገለግለው፣ መልካም እንዲሆንልህና ዛሬ እኔ የምሰጥህን ትእዛዞችና ሥርዐቶች እንድትጠብቅ አይደለምን?›› (ዘዳ. 10፡12-13)።

**ፍትህ ምህረትና ትህትናን ከእኛ ይሻል**

‹‹ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው?
ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?››(ሚኪያስ 6፡8)

**እግዚአብሔርን መፍራት (1ጴጥ. 2፡17)**

***እግዚአብሔርን መፍራት እርሱ ታላቅ አምላክ፡ ኃያልና የሚያስፈራ መሆኑን ከመረዳት ይመነጫል***

እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን ምህረት መረዳት ስንጀምር እውነተኛ ፍቅር ምን መሆኑንና እግዚአብሔር ምን ያህል ጥልቅ በሆነ ፍቅር እንደሚወደን ማየት እንችላለን። በምህረቱ ፊት ስንሆን እርሱ ምን ያረገን ይሆን (ምን ይደርስብን ይሆን) የሚለው ፍርሀት ይለወጥና እርሱን ወደማክበርና በእርሱ ወደመደነቅ ውስጥ እንገባለን። እንደ ኃጢአታችን ቢሆን ኖሮ ቅጣቱ የከፋ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለሚፈልጉት ሁሉ ፍቅሩንና ምህረቱን ማሳየት መረጠ፤ ወደደ። ‹‹እግዚአብሔርን የሚፈሩ እነማን ናቸው? እነርሱ መከተል የሚገባቸውን አካሄድ እንዲመርጡ እርሱ ያስተምራቸዋል›› (መዝ. 25፡12)

**እግዚአብሔርን እንደማንነቱ ስናውቀው ለእርሱ ያለን የአክብሮት ፍርሃታችን ይጨምራል**

እግዚአብሔርን መፍራት ማለት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማወቅ ማለት ነው፤ ይኸውም እርሱ ቅዱስና ሁሉን ቻይ ጻድቅና ሁሉን አዋቂ ጥበበኛ መሆኑን መረዳት ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ማንነት በትክክል ስንረዳ፡ የራሳችን እውነተኛ ማንነት ማለትም ኃጢአተኛና ደካማ፡ ያለ እርሱ ምንም እንዳልሆንንና ምስኪንነታችን ይገለጥልናል። የእግዚአብሔርና የእኛን ማንነት ስንረዳ (የእርሱን ታላቅነትና የእኛን ኢሚንትነት ሲገባን) በእግሩ ስር በትህትና ተደፍተን አክብሮታችንን እንገልጽለታለን፤ ያን ጊዜ ነው እርሱ የመረጠውን መንገድ የሚያሳየን።

**እግዚአብሔርን መፍራት እርሱን ይበልጥ ወደማወቅ ደረጃ ያመጣናል**

‹‹ጌታ ለሚፈሩት ወዳጃቸው ነው›› (መዝ. 25፡ 14) እንደሚለው ትልቅ ክብር የሚሰጡትን ወደ ራሱ ያቀርባቸዋል ለዘላቂ ወዳጅነት ይጋብዛቸዋል። ከአምላክ/ከፈጣሪ ጋ/ ያለንን ወዳጅነት የሚተካከል/የሚወዳደር/ የለምና እርሱን ባከበርነው ቁጥር ከእርሱ ጋር ያለን ዘላለማዊ ወዳጅነታችን ያድጋል።

**እግዚአብሔርን መፍራት ማለት በእርሱ ምክንያት ፍርሃት ውስጥ መግባት ማለት አይደለም**

ሙሴም ለሕዝቡ እንዲህ አላቸው፡ ‹‹አትፍሩ፡ ሊፈትናችሁ ኃጢአትንም እንዳትሰሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ እንዲሆን እግዚአብሔር መጥቷልና›› (ዘጸ. 20፡20)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ ‹‹አትፍሩ›› የሚል ቃል እናገኛለን። ይህም ያለው እግዚአብሔር ሕዝቡን ማስፈራራት ፈልጎ ሳይሆን እሥራኤላውያን ታላቅ ኃይሉን በመመልከት እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንዲያውቁና እንዲታዘዙት ለማድረግ ነበር፤ በሚታዘዙበት ሰዓት የእርሱ ኃይል አብሮአቸው እንዲሆን ፈቃዱ ነበር። እግዚአብሔር ከፍርሃት ይልቅ በፍቅር እንድንከተለው ይፈልጋል፤ ፍርሃትን ለማሸነፍ ፍቅሩን ይበልጥ ማሰብ ይኖርብናል፤ ምክንያቱም ‹‹ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም›› (1ዮሐ. 4፡18)።

ይቀጥላል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራዎች ኮሚሽን ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**‹‹እስራኤል ሆይ፤ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? አምላክህን እግዚአብሔርን እንድትፈራው፣ በመንገዶቹ ሁሉ እንድትሄድ፣ እንድትወድደው፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ እንድታገለግለው፣ መልካም እንዲሆንልህና ዛሬ እኔ የምሰጥህን ትእዛዞችና ሥርዐቶች እንድትጠብቅ አይደለምን?›› (ዘዳ. 10፡12-13)**

# ቤተሰብ



በክቡር አቶ አርጋው ፋንቱ

# የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ክስተት ለእምነታችን ጽናት

*ያለፋትን ሃምሳ አምስት ቀናት ከሞላ ጎደል (በጽናት የተሳተፉትንና የፈጸሙትን ይህ 'ከሞላ ጎደል' ቃል አይመለከታቸውም) በፆም፣ በጸሎትና በበጎ ሥራ በመትጋት፤ የእምነታችን ሥርዓት በሚጠይቀውም መልኩ በየሣምንቱ በመስቀል መንገድ ጸሎት ተሳትፈናል። የክርስቶስን ሥቃይና ፈተና፣ እስከመስቀል ሞት ያደረሰውን የሰውን የክፋት ጥግም በስፋት አስተንትነናል፤ የየራሳችንንም ውስንነቶችና የመተላለፍ ድርሻ በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አሰላስለናል።*



ይህንን ሁሉ አልፈን ዛሬ ላይ ደርሰን (ሰላሙንና ጤናውን አግኝተን የደረስን ሁሉ) "እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!" እየተባባልን እንገኛለን። ለመሆኑ "ለብርሃነ ትንሣኤው መድረስ ምንድር ነው?" ብለን ጠይቀን ይሆን! ካልሆነም ዛሬ ላይ ጠይቀን መልሱን ለየራሳችን እንስጥ። ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ እንደተማርነው፣ እንዳነበብነውና እንዳመንነው፡ የክርስቶስ ትንሣኤ የእምነታችን ምሰሶ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም "ክርስቶስም ካልተነሣ ስብከታችን ዋጋ ቢስ ነው፤ እምነታችሁም ከንቱ ነው" (1ቆሮ.15፡14) በማለት ያጸናዋል። አራቱ ወንጌላትም (የተለያየ በሚመስል አገላለጽ ቢሆንም) መግደላዊት ማርያምና ሌሎች ሴቶች የመቃብሩን ባዶነት አይተው ተመልሰው የክርስቶስን ትንሣኤ ለሐዋርያቱ እንዳበሠሩ ይነግሩናል። ሐዋርያው ጴጥሮስም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ በድፍረት ወደ አደባባይ ወጥቶ ትንሣኤውን መስክሮአል፡ እንዲህ በማለት "...በዐመጸኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳው፤ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና።" (ግ.ሐዋ.2፡23-24)።

ብዙዎች እንደሚስማሙበትና እንደሚመሰክሩት የክርስትና እምነት አንዱ እውነታ በታሪካዊ ክስተቶች የተሞላ መሆኑ ነው። ከዘፍጥረት ጀምሮ ያሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክስተቶች ታሪካዊ መሠረት እንዳላቸውም እሙን ነው። የቤተክርስቲያን በክርስቶስ መመሥረትም ታሪካዊ እውነታ ነው። እንዲህ፣ እንዲህ እያልን ስንመጣ የክርስቶስ ትንሣኤም ታሪካዊ መሠረቱና እውነታው ነው፡ ዛሬ ላይ እኛም በእምነት የተቀበልነው፣ የሕይወት ጉዞአችን አካልም ያደረግነው።

ይህንን የበለጠ ለመረዳት ከላይ በትንሹ ወደ ነካሁት የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት እንመለስ። ሐዋርያው በመልዕክቱ "እኔ የተቀበልሁትንና ከሁሉ በላይ የሆነውን ለእናንተ አስተላልፈአለሁ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡ " (1ቆሮ.15፡2-4) ይላል። እዚህ ላይ እንድናተኩር የፈለግሁት የሐዋርያው የጳውሎስን የአገላለጽ እውነታ ነው - "እኔ የተቀበልሁትን" የሚለውን። ይህንን አባባል በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል።

## የጸሎት ሐዋርያነት

ግንቦት

ለወንዶች እና ሴቶች ተመካርያን ህንፀት እና ለሴሚናርያን እንፀልይ

**ለወንዶች እና ሴቶች ገዳማውያን እና ለሴሚናርያን የጥሪ ጉዟቸውን በሰብአዊነት፣በሐዋርያዊ ስራ፣ በመንፈሳዊነት እና በማህበረሰባዊ ህንፀት ታማኝ የወንጌል ምስክሮች እንዲሆኑ እንዲመራቸው እንፀልይ።**

MAY

For the Formation of Men And Women Religious, and Seminarians

Let us pray that men and women religious, and seminarians, grow in their own vocational journey through human, pastoral, spiritual and community formation,that leads them to be credible witnesses of the Gospel.

### የማቅረቢያ ጸሎት

ኢየሱስ ሆይ በእመቤታችን

በቅድስት ድንግል ማርያም ንፁህ ልብ አማካይነት የዚህን ቀን ጸሎቴን ፣ሥራዬን፣ ደስታዬን፣ ሐዘኔንና ሥቃዬን በመላው ዓለም ከሚቀደሰው ቅዳሴ ጋር አንድ አድርጌ ለአንተና ለቅዱስ ልብህ ሐሳቦች አቀርባለሁ፤ ለነፍሳት ደኅንነት፣ ለኃጢአት ካሣና ለክርስቲያኖች አንድነት፣ ለጳጳሳትና ለጸሎት ሐዋርያነት ማኅበር በተለይም ለዚህ ወር በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለተሰጡት ሐሳቦች አቀርባለሁ።

*ማስተንተኛ*

*ተመካርያን እና ሴሚናርያን በቀጣይ ቤተክርስቲያንን የማስተዳደር ስራ የሚረከቡ ናቸው፤ ህንፀታቸውም ወሳኝ የሚሆነው ለዚህ ነው። በተለይ ለነሱ የምንፀልይበት ምክንያትም ለዚያ ነው። በሚያገኙት የጠለቀ የመንፈሳዊነት እና የሐዋርያዊ ስራ በደንብ እንዲታነፁ እና የመንፈስ ቅዱስ እገዛም እንዲበዛላቸው እንፀልይ።*

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዴት ባለ ሁኔታ ኢየሱስን እንዳገኘ/እንደተቀበለ እዚህ ላይ መተረኩ አስፈላጊ አይመስለኝም - ለቀባሪ ማርዳት እንዳይሆንብኝ። ሆኖም ግን ታሪኩን ለመድገም ግብረ ሐዋርያት ም.9፡ 1-19 ማየቱ አይከፋም። በአጭሩ የክርስቶስ ጠላት የነበረው (እንደሚገባኝና ብዙዎች እንደሚቀበሉት ከጭካኔ የተነሣ ሳይሆን ለአይሁድ እምነቱ ካለው ቀናዕነት ነው) ጳውሎስ የክርስቶስ የትንሣኤው መስካሪ ሆኗል። የተቀበለውም ቀድሞ በሚያዩት ዓይኖቹ ሳይሆን ከዓይኑ ላይ የክፋት ቅርፊት ከተነሳለት በኋላ ነው፡ "ወዲያውኑ እንደ ቅርፊት ያለ ከዓይኑ ወደቀ፣ ያን ጊዜም አየ፡"(ቁ.18) እንደሚለው። ይህ የአባበሉ የመጀመሪያ ሁኔታ ነው።

ዛሬ ላይ በስንት የክፋት ቅርፊቶች ዓይኖቻችን ተሸፍነው፣ እነርሱን ለማንሳት እየታገልን ይመስለኛል የዐርባ ፆም ጊዜያትን በብርቱ ተጋድሎ ያሳለፍነው። ጳውሎስ አልጠቀሰውም እንጂ ጆሮዎቹስ ስንት ክፋቶችን በተሳትፎ ወይም በቁጭት አድምጠው ይሆን? ዛሬ ላይስ በተለይም ባለፋት የዐርባ ፆም ወራት ጆሮዎቻችን ስንት ክፋቶችን (ከቅርብም ሆነ ከሩቅ) እየሰሙ አልፈው ነው የክርስቶስን ትንሣኤ የምናከብረው?

ጳውሎስ ከእንደዚያ ያለ ሁኔታ ወጥቶ በፍጹም መለወጥ ተለውጦ "ከሁሉ በላይ የሆነውን ለእናንተ አስተላልፈአለሁ" ብሎናል። እኛም ዛሬ የክርስቶስን የትንሣኤ በዓል እውነትነት ስናከብር "ለኛ ከሁሉ በላይ የሆነው እውነት የቱ ነው?" ብለን እንድንጠይቅ ጊዜው ግድ ይለናል።

በሁለተኛ መልኩ ጳውሎስ የተቀበለውና የመሰከረው የክርስቶስ ትንሣኤ፡ እርሱ እንደ ሐዋርያቱና እንደ ሴቶቹ ታድሎ፣ በመቃብሩ ሥፍራ ተገኝቶ ያየውን ሳይሆን የተገለጠለትን፣ የሰማውንና በቅዱሳት መጻሕፍት ያገኘውንና ያመነውን ነው። ዛሬ ላይ እኛም ሳናይ ያመንን "ጳውሎስስ (ትንሣኤውን በአካል ባለማየቱ) ከኛ በምን ይሻላል?" ብለን አጉረምርመን ይሆናል። ብዙ የሚያደናግሩና እምነትን የሚፈታተኑ ነገሮችና ሙግቶች በበዙበት ዘመን ለምንኖር ለኛ ይህ ተፈታታኝ ሀሳብ አይቀሬ ይመስለኛል። ሆኖም ግን ጳውሎስ እስከ መጨረሻ ባለው ጽናቱና ራሱን ለተገለጠለት ክርስቶስ ብርቱ ወታደር ሆኖ በመዝለቁ በእጅጉ ይበልጠናል። ዛሬ ላይ በየቤቱ፣ በየቤተሰቡና በየገዳማቱ ያለነው ምን ያህሉን የጳውሎስን የእምነት ጸናት ይዘን ይሆን ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።

በመቋጫም ወቅትን ጠብቆ በዓልን ማክበር ብቻ ሳይሆን፡ የበዓል አከባበራችን እንደጳውሎስ በእውነተኛ መለወጥ ተለውጦ፣ የእምነታችን ምሰሶ የሆነውን የትንሣኤውን እውነትነት በእምነት አጽንቶ፣ በዓይኖቻችን ላይ ያሉ የክፋት ቅርፊቶችን በርሱ ፀጋ አውልቆ፣ ጆሮዎቻችን ከሚሰሙት የክፋት ድስኩሮች በሚዛናዊነት ርቆ ቢሆን ይመረጣል ብዬ አምናለሁ። በዚህ መልኩ ትንሣኤውን የምናከብር ከሆነ በእውነትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ክስተት ለእምነታችን ጽናት አቅም ይሰጠናል። እንደ ጳውሎስም ለመመስከር ጽናቱን አይነፍገንም። እስከ መጨረሻውም እንድንጸና የትንሣኤው ጌታ በማይቆጠብ ፀጋው ይጎብኘን። አሜን። **እንኳን አደረሰን!**

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት እናከጤና ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**‹‹እግዚአብሔርን የሚፈሩ እነማን ናቸው? እነርሱ መከተል የሚገባቸውን አካሄድ እንዲመርጡ እርሱ ያስተምራቸዋል›› (መዝ. 25፡12)**



በክቡር አባ ፊሊጶስ ደንድር
የእምድብር ሃገረስብከት ካህን

# መቃብር ይዞ አላስቀረውም



*ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ነውና መቃብር ይዞ አላስቀረውም፣ ትንሣኤ ነውና ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን አልነበረውም በመሆኑም መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ሞትን ድል አድርጎ መውጊያውንም ሰብሮ በኃይሉ ተነስቷል። ሞት ሆይ መውጊያህ የታለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የታለ» ተብሎ በትንቢት በተነገረው መሠረት ገዥውንና ኃያሉን አሸንፎ መውጊያውን ሰብሮ ጌታችን ተነስቷል።*

ክርስቶስ ከሙታን መካከል ተለይቶ መነሣቱ ታላቅ ክስተት ስለነበር አይሁድን ሕብረት ፈረካክሶታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከስቅላቱ በፊት የትንሣኤውን መልካም ዜና አብስሯል። ለደቀመዛሙርቱም በተደጋጋሚ የሰው ልጅ መከራ እንደሚደርስበት፣ የሞት ፍርድ እንደሚገጥመው፣ በአሕዛብ እጅ ተላልፎ እንደሚሰጥ በሚዘብቱበት አይሁድ እጅ ውስጥ እንደሚገባ በመጨረሻም ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ተናግሮ ነበር።

ጌታችን መከራውንና ሞቱን መናገር የጀመረው ገና በደብረ ታቦር ተራራ ብርሃነ መለኮቱን ከገለጠ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጡ ነበር። ከተራራውም ሲወርድ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዟቸው (ማር 9፡9) ማቴ 16፡21 ወደ ገሊላም ሲሄዱ በተለያየ አጋጣሚ ይነግራቸው ነበር። በመጨረሻም ግን የጸሎተ ሐሙስ ዕለት በድጋሚ ነገራቸው ሐዋርያትም ስለ ራሳቸው የዓለም ሹመት አስበው አዘኑ፣ ሁሉን ትተን ተከትለነው ይሾመናል ስንል ጥሎን ሄደ ብለው አዘኑ (ማቴ 20፡20) ስለ ፍቅር ስለ ትህትናው አዘኑ፣ ጌታችን ምንም እንኳን የሰውን ሥጋ ለብሶ በመካከላቸው ቢመላለስም በጥንተ ተፈጥሮ ፈጣሪያቸው አባታቸው ከመሆኑም ባሻገር በመካከላቸው በተመላለሰበትም ዘመን የእጁን ተአምራት አይተዋል፣ የቃሉን ትምህርት ሰምተዋል፣ መግቧቸዋል በመከራ በማዕበል ሰዓትም አጽናንቷቸዋልና ሲለያቸው ግን አዘኑ ጥሪያቸውን አላወቁም ነበርና አዘኑ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያቱን ወክሎ ሁሉን ትተን የተከተልንህ እኛ እንግዲህስ ምን እናገኝ ይሆን? ብሎ ጠይቋል። (ማቴ 19፡28) ጥሪያቸው ለሰማያዊ እንደነበር አላስተዋሉምና አዘኑ ሞቱን እንጂ ትንሣኤውን አላስተዋሉም አላመኑም ነበርና አዘኑ «የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተላልፎ ይሰጣል ይገድሉታልም በሦስተኛውም ቀን ይነሣል» (ማቴ 16፡21) ነበር ያላቸው። እንዲሁም «ከተነሣሁ በኋላ በገሊላ እቀድማችኋለሁ ብሏቸው ነበር» ማር 14፡28 ከዚህም በተጨማሪ የዮናስን ምልክት መሆን በምሳሌ ገልጦላቸው ነበር (ማቴ 12፡38) ነገር ግን መጻሕፍትን ባላማስተዋላቸው አዘኑ እሱ ግን ሐዘናችሁ ወደ ደስታ ይቀየራል፣ ዮሐ 16፡20 በማለት በምሳሌ አጽናናቸው ሴት ልጅ ልትወልድ በቀረበች ጊዜ ታዝናለች ከወለደች በኋላ ግን ኃዘኗ ወደ ደስታ ይለወጣል(ማቴ 16፡21)

ፈሪሳውያን ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትንሣኤው የተናገረውን አውቀው ወደ ጲላጦስ ቀረቡና እንዲህ አሉት ገዥ ሆይ ያ አሳች ገና በሕይወቱ ሳለ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አለን እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ የኋለኛይቱ ስህተት ከፊተኛይቱ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩ እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት (ማቴ 27፡62-64) አይሁድ ፊተኛይቱ ስሕተት ብለው ቅጽል ከሰጡትና ክርስቶስ ከሰጣቸው መመሪያዎች ይልቅ ትንሣኤው በእነርሱ ላይ አደጋ የሚያመጣባቸው መስሎ እንዲታያቸው ያደረጋቸው አስፈሪ ትዕይንት ምንድን ነው?

የክርስቶስ ትንሣኤ የእርሱን እውነተኛነት ያረጋገጠና ትንቢቶች ሁሉ እውነተኛ መሆናቸውን የገለጠ ነው ትንሣኤው እርሱ ኃያል መሆኑን አረጋግጧል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ስቅላት የደረሰበትም የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን እንጂ ደካማ ስለሆነ አልነበረም እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሰዎች በእርሱ ላይ የበረታና የጠበቀ እምነት እንዲኖራቸው መርተዋል። አይሁድ የክርስቶስን መነሣት ለመቃወም የሚችሉበትን ጥንቃቄ ሁሉ አድርገዋል። ሌላው ቢቀር በመቃብሩ መግቢያ ላይ ትልቅ ድንጋይ በማንከባለል ገጥመውት ሄደዋል። እነርሱ በድንጋይ ላይ ማኅተም በማድረግ መቃብሩ እንዲጠበቅ ከማድረጋቸውም ሌላ ጠባቂ ዘበኞች አስቁመዋል። (ማቴ 28፡66) የሚገርመው ግን ይህን ሁሉ ከመዘጋጀት ቀን በኋላ በሰንበት ምሽት በማድረጋቸው ምንም አላፈሩም ነበር፣ መድኃኒታችን ክርስቶስ የዓይነ ሥውሩን ዓይኖች በሰንበት ቀን ስለፈወሰ ግን ከሰውት ነበር» (ዮሐ 9፡14-16) ።

በድንጋይ ላይ የታተመው ማኅተምና በባዶው መቃብር ደጃፍ ላይ የቆሙት ጠባቂዎች የክርስቶስ ትንሣኤ እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል፣ በመሆኑም ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መካከል በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ተለይቶ ተነስቷል። የጌታችን ትንሣኤ የቤተ ክርስቲያንን ምሥረታ እውን አድርጓል ፤ እርሱ ከሞት ባይነሣ ኖሮ የቅርብ ተከታዮቹ ተስፋ ቆርጠው ወደ ቀድሞ ተግባራቸው በተመለሱ ነበር (ዮሐ 21፡1-7) አማንያንም በተበተኑ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን አስረግጦ ሲያስተምር «ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣም ክርስቶስ ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ናት እምነታችንም ደግሞ ከንቱ ናት እስካሁንም ድረስ በኃጢአታችን ነን፣ በክርስቶስ ያንቀላፉትም ጠፍተዋል በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን ፡ አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኲራት ሆኖ ተነስቷል» (1ቆሮ 15፡12-20)

ስለ“ፍቅርና ሰላም ጋዜጣ”
አስተያየት ካለዎት
በስልክ ቁ.
(0111) 55 03 00
በመደወል ለፍቅርና ሰላም
ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያካፍሉን!






ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

«አትፍሩ፡ ሊፈትናችሁ ኃጢአትንም እንዳትሰሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ እንዲሆን እግዚአብሔር መጥቷልና»
(ዘጸ. 20፡20)

# የቃሉ ውበት

# “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! ከእነዚህ ይበልጥ ትወደኛለህን?”
## (ዮሐ 21፡ 15)

በክቡር አባ ዳንኤል አሰፋ (ዶ/ር)



**ሥርጉት፡-** የፋሲካ በዓል ሲከበር ሁል ጊዜ ትዝ የምትለኝ ማርያም መቅደላዊት ናት።
**ሳሙኤል፡-** እኔ ደግሞ ትዝ የሚለኝ ቅዱስ ጴጥሮስ ነው።
**ኀሊና፡-** በሉ፣ እያንዳንዳችሁ ምን ትዝ እንደሚላችሁ ተናገሩ።
**ሥርጉት፡-** መቅደላዊት ማርያም ኢየሱስን ወዷያው አለማወቋ ይገርመኛል።
**ኀሊና፡-** በመሠረቱ፣ ማርያም የሕይወቷ መሠረት የሆነውን ኢየሱስን ልትረሳ አልቻለችም። በፊት አየሱስ በመሞቱ ታለቅስ ነበር። አሁን ደግሞ አስከሬኑ ባለመኖሩ በጣም ደንግጣና አዝና እያለቀሰች ትፈልገዋለች። በዚህ ወቅት ነው፣ ሁለት ነጭ የለበሱ መላእክት “የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው” ያየችው።
**ጥበቡ፡-** እነዚህ ሁለት መላእክት የወረዱት እኮ የኢየሱስን ትንሣኤ እርግጠኛነት ሊያሳዩ ነው። ምስክርነታቸውም ትልቅ ትርጉም አለው። ኢየሱስን ሌቦች እንዳልወሰዱት፣ ይልቁንም ትንሣኤ ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ያመለክታል።
**ኀሊና፡-** ነገር ግን ማርያም ሌላ ሰው እንደመጣ ታወቃት። ያም ሰው አትክልተኛው መሰላት። የምታለቅስበትን ምክንያትም ከነገረችው በኋላም የኢየሱስን ሥጋ ወደሌላ ቦታ ወስዶት ይሆንን ብላ በማሰብ ያደረገበትን እንዲነግራት ጠየቀችው። ይህ ምንኛ ታላቅ እምነትና ፍቅር ይሆን? የጌታን አስከሬን ማግኘት አለብኝ በማለት ነበር የምትፈልገው። እሷ ግን ሳታውቀው ከአስከሬን የበለጠ ልታገኝ ነው።
**ጥበቡ፡-** አዎን፣ ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን በመጀመርያ አላወቀችውም ነበር። በስሟ ሲጠራት ነው ያወቀችው። ይህ የእርሷ ማወቅ በዮሐንስ 10፡ 3 ላይ የተጠቀሰውን ያስታውሳል፣ «ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።» ከእንግዲህ ትንሣኤውንና እርገቱን ማብሠር ነው የሚጠበቅባት። ከመስቀሉ በፊት ባለው ዓይነት እርሱን ልትይዘውና ልትመለከተው አያስፈልግም። እርሱ ወደ አባቱ ወደ አብ እየተጓዘ ነው።
**ሥርጉት፡-** በጣም አመሰግናለሁ።
**ሳሙኤል፡-** እኔ ደግሞ የማስታውሰው “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ትወደኛለህን?” ብሎ የጠየቀው ይገርመኛል።
**ጥበቡ፡-** ምንድን ነው የገረመህ?
**ሳሙኤል፡-** በታሪኩ መጨረሻ ላይ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ማቅረቡ ይደንቀኛል። ወይ መጀመርያ ላይ፣ ወይ ወደ መሃል ላይ ቢጠይቀው አይሻልም ነበር?
**ጥበቡ፡-** ይህ ጥያቄ እኮ የቀረበው ከትንሣኤ በኋላ ነው። ስለዚህ ከትንሣኤ በፊት ካለው ሁኔታ ትንሽ የሚለይ አይመስልህም?
**ሳሙኤል፡-** ቢሆንም፣ “ተከተለኝ” ብሎ ሲጠራውና ሲከተለው ስለሚወደው አይደለም እንዴ የተከተለው?
ጥበቡ፡- ወደ ኋላ ተመልሰን የምንመለከት ከሆነ፣ ጴጥሮስ ብዙ ነገርን አይቷል። ነገር ግን ያልገባውም ነገር እንደነበረ ይታያል። ባንድ በኩል ሌሎች ደቀ መዛሙርት ዝም ባሉበት “አንተ ክርስቶስ ነህ” ብሎ መስክሯል። በሌላ በኩል ደግሞ “ይህ መሆን የለበትም” በማለት ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ለመከልከል ሞክሯል፤ ወይንም ለክርስቶስ መንገዱን ለማሳየት በመሞከሩ ክርስቶስ “በስተኋላዬ ሂድ” አለው። እንዲሁም ባንድ በኩል “ሕይወቴን” ለጌታ “እሰጣለሁ” ብሏል። በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቶስ በተያዘ ጊዜ ሸሽቷል። ጴጥሮስም የክርስቶስን ትምህርቱንና ተአምራቱን በግልጽ አይቶ ነበር። ከሌሎቹ በተሻለ መልኩ መሢሕነቱን ና የእግዚአብሔር ልጅነቱን አስተውሏል።
**ሳሙኤል፡-** ታዲያ ለምንድን ነው የሸሸው?
**ጥበቡ፡-** ኢየሱስን በሚይዙበት ወቅት ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጎን ለመሰለፍ መሞከሩን የሚያመለክት ድርጊት ፈጽሞ ነበር (ዮሐ 18፡10)። ሰይፍን በመምዘዝ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ እስከመቁረጥ ደረሰ። ጴጥሮስ ይህንን ያደረገው ለኢየሱስ እዋጋለሁ ወይም ኢየሱስን አስጥላለሁ በሚል ተነሣሽነት ይመስላል። ምንም እንኳን የኢየሱስ መንግሥት በሰዎች ሰይፍ የሚጠበቅ ባይሆንም ጴጥሮስ በየዋህነት ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር ለመግለጽ ሞክሮ ነበር። ኢየሱስንም እስከ መጨረሻው ለመከተል ሞክሮ ነበር። በሊቀ ካህናቱ ግቢ ከገባ በኋላ ግን የበፊቱ ድፍረት ይሁን ወኔ ጠፋ። በፍርሃት ተውጦ ቀድሞ ድጋፉን ለመግለጥ ሰይፍ መዘለት ሲያበቃ አሁን ደግሞ ኢየሱስን እንደማያውቅ ሰው ሆነ። “አላውቀውም” ሲል ካደ።
**ኀሊና፡-** የምናስበውና በተግባር የምናውለው ላይጣጣም ይችላል። በተለይም ደግሞ ፍርሃት የሚያስከትለውን ነገር መገመት ከባድ ነው። ሰው ሲደነግጥ ያለጠበቀው ነገር ሊከሰት ይችላል። ሌላ ዐቢይ ጉዳይም አለ። እሱም ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ብዙ ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት መሢሕ ይጠብቅ ነበር የሚለው ነው።
**ሳሙኤል፡-** አልገባኝም።
**ኀሊና፡-** ቅዱስ ጴጥሮስንም ጨምሮ፣ ብዙ ሰዎች ይጠብቁት የነበረው መሢሕ በጉልበት ሮማውያንን አስወግዶ ሕዝቡን ከቀኝ ግዛት ነጻ ያወጣል ብለው ነበር። እግዚአብሔር የቀባው መሢሕ ይሰቃያል ብለው በጭራሽ አልጠበቁም ነበር። ጴጥሮስም “ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ የለብህም” ያለበት ምክንያት ከዚሁ ጋር የሚቀራረብ ነው። ነገር ግን ጴጥሮስ ክዶ አልቀረም። ክህደቱንም ለማስተባበል ሆነ፣ ምክንያት ለመስጠት አልሞከረም። ይልቁንም ምርር ብሎ በማልቀስ ተመለሰ። የሰውን ደካማነትና ወዳቂነት አሳየ። የትሕትናና የፍቅር ምሳሌንም ሰጠ። ጥፋትን አምኖ በመጸጸት ትልቅነትን አሳየ። በእንባው የምሕረትንና የፍቅርን መዛመድ አሳየ። መስቀል ክብሩ የሆነ ንጉሥ፣ በጽድቅ የተዋበ ንጉሥ፣ በፍቅር የሚያንጸባርቅ ንጉሥ፣ ምሕረት ኃይሉ የሆነ ንጉሥ፣ ትሕትና ድሉ የሆነ ንጉሥ ጴጥሮስን እንደገና ለትልቅ ነገር ይጠራዋል!
**ሳሙኤል፡-** ስለዚህ ጴጥሮስ ገና ያልገባው ነገር ነበር ማለት ነዋ?
**ጥበቡ፡-** ይመስለኛል። ይህ ጥርጣሬ፣ ግራ መጋባት፣ ከድንጋጤ ጋር ተደምሮ እንዲሸሽ ያደረገው ይመስለኛል።
**ሥርጉት፡-** ቢሆንም እርግጠኛ ሆኖ የሰውን ሐሳብ መረዳት አያዳግትም?
**ጥበቡ፡-** ለዚህ እኮ ነው ይመስለኛል ያልኩት።
**ሳሙኤል፡-** “ትወደኛለህን” ወደሚለው ትርጉም ገና አልመጣንም።
**ኀሊና፡-** ለዚህ ከሞት የተነሣው የኢየሱስንና የሐዋርያትን ሁኔታ ማጤን ያስፈልጋል (ዮሐ 20፡19-23)። ደቀ መዛሙርቱ፣ ጴጥሮስም ጭምር፣ በሩ በተዘጋ ቤት ይቀመጣሉ። የገጠማቸው አእምሮአቸው ከሚቀበለው በላይ ነው። የመቃብሩ ባዶ መሆን፣ የመቅደላዊት ማርያም ዜና፣ የጴጥሮስና ኢየሱስ የሚወደው ደቀመዝሙር መልእክት ግራ አጋብቷቸዋል። ታዲያ ይህ በእንዲህ እንዳል ሌላ ያልጠበቁት ነገር ይከሠታል። ኢየሱስ በመካከላቸው ተገኘ። ዓለም ሊሰጠው የማይችለውንም ሰላም አቀረበላቸው። የእጆቹንና የጎኑን ቁስል አሳያቸው። እነሱም ቁስሉን አይተው አወቁት።
**ጥበቡ፡-** ከትንሣኤ በኋላ እንግዲህ ጴጥሮስ “በጎቼን ጠብቅ” የሚል ትእዛዝ ቀረበለት። ነገር ግን የኢየሱስን በጎች ለመጠበቅ ከምንም በላይ ኢየሱስን መውደድ ያስፈልጋል። መልካም እረኛ ኢየሱስ ነው (ዮሐ 10)። ነገር ግን ይህንን ልዩ መለኮታዊ ሀብት ለጴጥሮስ ማስተላለፍ ወደደ። በጎችን መጠበቅ ማለት የእረኝነት አገልግሎትን ማከናወን ማለት ነውና። ውብ ትእዛዝ፣ ውብ ስጦታ!
**ሳሙኤል፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**«ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።»**
**(ዮሐ. 10፡ 3)**



በክቡር ካቲኪስት ወርቁ ጦጤ
ከኮንሶላታ ማርያም ቤተ ጸሎት

# “ኃጢአትን ማድረግ እየቻለ የማያደርግ ብፁዕ ነው”

## (ሲራ. 31፡10)

እግዚአብሔር እኛ የሰው ልጆች የሆን ጽድቅን እንድንወድ፣ ኃጢአትን እንድንጠላ ይፈልጋል። ክፉ ብናደርግ ቅጣት መልካምና በጐ ሥራ ብንሠራ፤ ሽልማትና ከፍ ያለ ዋጋ እናገኛለን። ዋጋውም የብፅዕና የማዕረግ ስም ካባ እንለብሳለን። እግዚአብሔር ምንም እንኳ ኃጢአትን እንድንጠላ፣ ጽድቅን እንድንወድ ቢፈልግም በግድ “መልካምና በጐ” አድርጉ፤ “ክፉን” አታድርጉ ብሎ አያስገድደንም። ምክንያቱም ነጻ አድርጐን ነው የፈጠረን። ጌታ ሲፈጥረን ነጻነትን የሚያህል ከፍ ያለ ስጦታ አጐናጽፎናል። በሽልማትም አጊጦ ነው የፈጠረን። በእርሱ ፊት መልካምና መጠፎ በጐና ክፉ ሥራ ለማድረግ እንድንችል ከነጻነት ጋር ሙሉ አርነት ሰጥቶናል። ግርማ ሞገስም እንደሚሰጥ ልብስ አልብሶናል።

እግዚአብሔር አባታችን ለእኛ ለልጆቹ ሁለት የሕይወት ምርጫ ሰጥቶናል። ይኸውም፡ - “ከኃጢአት ባርነት ተላቀን መልካም ሥራ በመሥራት ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት” ወይም “ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጪ ርቆ በመሄድ ኃጢአትን በመሥራት የሰይጣን ሥራ በሥጋችን ተላብሰን መጨረሻው ገሀነመ እሳት ለሚጠብቀው ሰይጣን ከእርሱ ጋር ወደ ገሀነመ እሳት መውረድ ነው”። እያንዳንዳችን ሕሊናችን ሳይዋሸን ጥሩ ስንሠራ የጥሩ ዋጋ ሽልማት እና መጥፎ ከሠራን ለሠራነው መጥፎ ሥራ ዋጋችን ከእግዚአብሔር እንደምንቀበል እናውቃለን። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ የሚለን “ሥጋውን ለማስደሰት የሚዘራ ከሥጋው ሞትን ያጭዳል መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ከመንፈስ የዘላለም ሕይወትን ያጭዳል” (ገላ. 6፡8)።

እግዚአብሔር በመጽሐፈ ሲራክ ሲያስተምረን ሰው መጥፎ ለማድረግ ነጻ ቢሆንም ክፉ ለማድረግ በነጻነቱ የማይጠቀም ሰው ክፉ ነገር ከማድረግ በመቆጠብ ያመሰግነዋል። የሚያመሰግነውም “ብፁዕ” የሚል የተጋድሎ የመንፈሳዊ የማዕረግ ስም ይሰጠዋል። ሳኦል ዳዊትን ለመግደል በተሰደደ ጊዜ ዳዊትን በዓይኑ ለማየትም በጠላው ጊዜ የሳኦል ልጅ ዮናታን አባቱ ዳዊትን ለመግደል ክፉ መንፈስ በተላበሰበት ጊዜ ዮናታን ዳዊትን እጅግ ይወደው ስለነበር አባቱ ዳዊትን እንዳይገለው ስለፈለገ እንዲህ እያለው ለዳዊት ነገረው፡ - “አባቴ ሊገድልህ አቅዷል ስለዚህ እባክህ በነገው ማለዳ ይህ ክፉ ሥራ እንዳይደርስብህ ተጠንቀቅ ተደብቀህ ባለህበት እርሻ ቦታ ወደ አባቴ ቀርቤ ስለ አንተ እነግረዋለሁ”። (1ሳሙ. 19፡2-3)። ነገር ግን ዳዊት ሳኦል ሊገድለው እንደሚፈልግው እያወቀ፣ ከእርሱ ለመሸሽ በሥጋ ብዙ ውጣ ውረድም ቢያይም፤ ዳዊት ሳኦልን ሊበቀለው ወይም መልሶ ለማጥፋት ልቡ አልከጀለም። ወይም አልፈለገም።

እግዚአብሔር ሳኦልን በዳዊት እጅ ላይ ቢጥልለትም ዳዊት ሳኦልን ሊገድለው አልፈለገም። ዳዊትም ሳኦል በእጁ ሲወድቅ የልብ ቅንነት ስላለው ሳኦልን ከመግደል ይልቅ ምህረት በተሞላ አንደበት እንዲህ አለው፡- “እግዚአብሔር ቀብቶ ባነገሰው በጌታ ላይ እጄን ከማንሳት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ በዚህም አባባሉ በሳኦል ላይ አደጋ እንዳይጥሉበት ዳዊት ተከታዮቹን ከለከላቸው” (1ሳሙ. 24፡6-7) በድጋሚም ዳዊት ሳኦልን እንዲህ አለው፡- “እግዚአብሔር የቀባህ ንጉሥ ነህና አኔ በጌታዬ ላይ እጄን አላነሳም ብዬ ራራሁልህ አባቴ ሆይ እነሆ ከካባህ ላይ ቆርጬ የያዝኩትን ጨርቅ ተመልከት ታዲያ እኮ ልገድልህ እችል ነበር ነገር ግን ይህን በማድረግ ፈንታ የልብስህን ጫፍ ቆረጥሁ በአንተ ላይ ለማመጽም ሆነ በአንተ ላይ ጉዳት ላደርስብህ አለመፈለጌን በዚህ መረዳት ትችላለህ”። (1ሳሙ. 24፡ 10-11)። ቃሉን በማስተዋል አንብቡት።

ስለዚህ ከዳዊት ሕይወት የምንማረው እኛም የሚያሳድዱንን ሰዎችን ከመበቀለ ይልቅ ለእነዚያ ሰዎች መራራትና ከልባችን ይቅርት ማድረግ እንደሚስፈልገን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል፤ እኛ የልብ ቅንነት ካለን እግዚአብሔር የልባችንን ቅንነት አይቶ ከጠላታችን እጅ (ከሚያሳድዱን፣ የሰይጣን መንፈስ ከተላበሱ ሰዎች) እጅ ያስመልጠናል፤ ይታደገናልም። (1ሳሙ. 19፡1-24፤20፣24) ምዕራፉን በማስተዋል አንብቡት።

ዮሴፍ የጲጢፋራ ሚስት ለዝሙት በጋበዘችው ጊዜ ማንም በቤት ውስጥ ስላልነበረ ዮሴፍ የሥጋ ፍላጐቱን ለማሟላት ቢፈልግ ኖሮ በዚያን ጊዜ ማመንዘር ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ይችል ነበር። ነገር ግን ኃጢአት መሥራት እየቻለ እግዚአብሔረ አምላኬን ታማኝነቴን ከማጐድል የሥጋ ፍላጐቴን መግደል አለብኝ ብሎ በገዛ ፈቃዱ ኃጢአትን ከመሥራት እራሱን ገታ (ታቀበ)። ዮሴፍም ታማኝነቱንም እንዲህ በማለት ለጲጢፋር ሚስት ይነግራታል።

ዮሴፍ ቁመናው የተስተካከለ መልካም ሰው ነበር። ከጊዜ በኋላ የጌታው ሚስት ዮሴፍን ተመልክታ ስለ አፈቀረችው “ና! ከእኔ ጋር አብረን እንተኛ” አለችው። እርሱ ግን ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልነበረም። (ዘፍ 39፡ 6-9) በመቀጠልም በዚያን ጊዜ የጌታው ሚስት ልብሱን ይዛ “ከእኔ ጋር ተኛ” አለችው እርሱ ግን ልብሱን እጇዋ ላይ ትቶላት ከቤት ሸሽቶ ወጣ። (ዘፍ. 39፡ 11-12)።

ዮሴፍ ከጊዜያዊ ደስታ ይልቀ አምላኬን አላሳዝነውም ታማኝነቴን እገልጥለታሁ ብሎ ቁርጥ ፈቃዱን ለጲጢፋር ሚስት ገለጸላት። ታማኝነቱንም በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም አሳያት። እኛም ወደ ራሳችን እንመለስና እያንዳንዳችን እራሳችንን እንጠይቅ። እኔ በዮሴፍ ቦታ ብሆን የእኔ ታማኝነት ምን ያህል ነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሕሊናችን ያውቀናል። የእኛን ሕሊና ደግሞ እግዚአብሔር ያውቀዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃሉ ለእኔም፣ ለአንተም፣ ለአንቺም፣ ለእርሶም፣ እንዲህ ይለናል፡- “ከእግዚአብሔር ፊት የሚሰወር ምንም ፍጥረት የለም፤ በእርሱ ዐይን ፊት ሁሉም ነገር ግልጥና ዕርቃኑን ሆኖ የሚታይ ነው፤ እኛም መልስ መስጠት የሚገባን በእርሱ ፊት ነው”። (ዕብ. 4፡13) ቃሉን በማስተዋል እናንበው።

“መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ” (ራዕ. 3፡22)። ኢየሱስም በቃሉ እንዲህ ይለናል፡- “ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ” (ማቴ. 13፡43፣ ማር. 7፡16)።

ስለዚህ የተወደዳችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ለቅድስና ተጠርተናል፤ ቅድስና ደግሞ የሚገኘው በሕይወታችን መንፈሳዊ የሕይወት ተጋድሎ ማድረግን ይጠይቀናል። ይህንን ተጋድሎ ለማድረግ ደግሞ ቁርጥ ፈቃድና ታማኝ መሆን አለብን። እኛም ቅዱሳን ተብለን እንድንጠራ ዕድል ተሰጥቶናል። ምክንያቱም ቃሉ እንዲህ ስለሚለን “እኔ አምላካችሁ አግዚአብሔር ቅዱስ ነኝ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ”። (ዘሌ. 19፡2)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱም የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ይልናል፡- “የጠራችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ አናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ”። (1ኛ ጴጥ. 1፡15)። ቃሉን በማስተዋል አንብቡት።

ስለዚህ በተሰጠን ዕድል ተጠቅመን እኛም ወደ ኃጢአት ከሚመራን መንገድ ተላቀን ወደ ቅድስና መንግድ መጓዙ ለሕይወታችን የተሻለ ነው። ኃጢአት ማድረግ ቀላል ነው ነገር ግን ኃጢአት ማድረግ እየቻልን ኃጢአትን አለማድረግ ደግሞ ትልቅ ተጋድሎ ስለሚጠይቀን ተጋድሎን በብርቱ ከተወጣን ሁላችንም ቅዱሳን እንባላለን። እኛም በእግዚአብሔር ፊት የምንዘራው ኃጢአትን መሥራት ብቻ ሳይሆን የቅዱሳንም ሥራ መሥራት እንችላለን። ለምሳሌ በተሰጠን ኃላፊነት ተጠቅመን ሰውን የማይጨቁን፣ ገንዘብ እያለው በገንዘቡ ልቡ ለማመነዘር የማይከጅል (ለዝሙት ልቡ የማይነሳሳ) እራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ እየተቻለ/ እየቻለች፣ እራሱን ዝቅ የሚያደርግ/የምታደርግ ገንዘብ ቦታ ሆኖ መስረቅ እየቻለ የማይሰርቅ ሰው.. እነዚህ ከተዘረዘሩ ውሰጥም ሆነ ውጪ መፈጸም እየቻለ/ እየቻለች የማይፈጽም ሰው ብፁዕ ነው/ናት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል፡- “ሰው የሚመሰገነው በግፍ መከራ ሲቀበል ስለ እግዚአብሔር ብሎ ቢታገስ ነው። ክፉ አድርጋችሁ ቅጣት ሳትቀበሉ ብትታገሱ ምን ምሥጋና ይኖራችኋል? ነገር ግን መልካም አድረጋችሁ መከራ ስትቀበሉ ብትታገሱ ከእግዚአብሔር ምሥጋና ታገኛላችሁ” (1ጴጥ 2፡19-20) ቃሉን በማስተዋል አንብቡት።

ነፃነትህን አውቀህ በጥንቃቄ መራመድ ጠበብና የማስተዋል ብልህነት ነው። በነጻነትህ እየተጠቀምህ በጐ ሥራ ብቻ መሥራት የሚመሰገን ሞያና ጐብዝና ነው። “ኃጢአትን ማድረግ ስትችል የማያደርግ ዕድለኛና ብፁዕ ነው” (ሲራ. 31፡10)። በዚህ መንገድ የሚሄድ ሰው ጠቢብና ብልህ በመሆን የሚከተለው የጽድቅ መንገድ ነው። እንግዲህ በሥራችን ሁል ጊዜ በዚህ መንፈስ ተመርተን እንሂድ። ነፃነታችንን ቅዱሳን አባቶቻችን ይጠቀሙበት እንደነበሩ እኛም በተሰጠን የቅድስና መንግድ በመሄድ እንጠቀምበት።

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሆይ እኛ አሁን ያለንበት ዘመን በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ስለሆነ በተሰጠን መንፈሳዊ ጸጋ በሰማነው በእግዚአብሔር ቃል እውነተኛ ታማኝ ክርስቲያኖች ሆነን በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና ጐዳና ዘወትር መጓዝ እንድንችል መንፈስ ቅዱስ የማስተዋልን ወይም የልቦና ጸጋውን በሕይወታችን ያብዛልን። አሜን።

እግዚአብሔር አባታችን ለሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላምን ይስጣት ለዓለማችንም ሰላምን ይስጣት የሰላሙ ንጉሥ ኢየሱስ ሰላሙን ያብዛልን።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከሶሻል ሪሃብሊቴሽን ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

‹‹ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል›› (ያዕ. 1፡5)።

LINK
No. 264 April 2024 P. O. Box 2454 Tel. (0111) 55 03 00 Addis Ababa

You are most welcome to
Subscribe and Advertise on LINK

## URBI ET ORBI MESSAGE OF HIS HOLINESS POPE FRANCIS

# EASTER 2024

*Central loggia of the Vatican Basilica Sunday, 31 March 2024*

*Dear brothers and sisters, Happy Easter!*
Today throughout the world there resounds the message proclaimed two thousand years ago from Jerusalem: "Jesus of Nazareth, who was crucified, has been raised!" (Mk 16:6).

The Church relives the amazement of the women who went to the tomb at dawn on the first day of the week. The tomb of Jesus had been sealed with a great stone. Today too, great stones, heavy stones, block the hopes of humanity: the stone of war, the stone of humanitarian crises, the stone of human rights violations, the stone of human trafficking, and other stones as well. Like the women disciples of Jesus, we ask one another: "Who will roll away the stone for us from the entrance to the tomb?" (cf. Mk 16:3).

This is the amazing discovery of that Easter morning: the stone, the immense stone, was rolled away. The astonishment of the women is our astonishment as well: the tomb of Jesus is open and it is empty! From this, everything begins anew! A new path leads through that empty tomb: the path that none of us, but God alone, could open: the path of life in the midst of death, the path of peace in the midst of war, the path of reconciliation in the midst of hatred, the path of fraternity in the midst of hostility.

Brothers and sisters, Jesus Christ is risen! He alone has the power to roll away the stones that block the path to life. He, the living One, is himself that path. He is the Way: the way that leads to life, the way of peace, reconciliation and fraternity. He opens that path, humanly impossible, because he alone takes away the sin of the world and forgives us our sins. For without God's forgiveness, that stone cannot be removed. Without the forgiveness of sins, there is no overcoming the barriers of prejudice, mutual recrimination, the presumption that we are always right and others wrong. Only the risen Christ, by granting us the forgiveness of our sins, opens the way for a renewed world. Jesus alone opens up before us the doors of life, those doors that continually we shut with the wars spreading throughout the world.

Today we want, first and foremost, to turn our eyes to the Holy City of Jerusalem, that witnessed the mystery of the Passion, Death and Resurrection of Jesus, and to all the Christian communities of the Holy Land. My thoughts go especially to the victims of the many conflicts worldwide, beginning with those in Israel and Palestine, and in Ukraine. May the risen Christ open a path of peace for the war-torn peoples of those regions. In calling for respect for the principles of international law, I express my hope for a general exchange of all prisoners between Russia and Ukraine: all for the sake of all!

I appeal once again that access to humanitarian aid be ensured to Gaza, and call once more for the prompt release of the hostages seized on 7 October last and for an immediate cease-fire in the Strip. Let us not allow the current hostilities to continue to have grave repercussions on the civil population, by now at the limit of its endurance, and above all on the children. How much suffering we see in the eyes of the children: the children in those lands at war have forgotten how to smile! With those eyes, they ask us: Why? Why all this death? Why all this destruction? War is always an absurdity, war is always a defeat! Let us not allow the strengthening winds of war to blow on Europe and the Mediterranean. Let us not yield to the logic of weapons and rearming. Peace is never made with arms, but with outstretched hands and open hearts.

Brothers and sisters, let us not forget Syria, which for thirteen years has suffered from the effects of a long and devastating war. So many deaths and disappearances, so much poverty and destruction, call for a response on the part of everyone, and of the international community. My thoughts turn today in a special way to Lebanon, which has for some time experienced institutional impasse and a deepening economic and social crisis, now aggravated by the hostilities on its border with Israel. May the Risen Lord console the beloved Lebanese people and sustain the entire country in its vocation to be a land of encounter, coexistence and pluralism. I also think in particular of the region of the Western Balkans, where significant steps are being taken towards integration in the European project. May ethnic, cultural and confessional differences not be a cause of division, but rather a source of enrichment for all of Europe and for the world as a whole.

I likewise encourage the discussions taking place between Armenia and Azerbaijan, so that, with the support of the international community, they can pursue dialogue, assist the displaced, respect the places of worship of the various religious confessions, and arrive as soon as possible at a definitive peace agreement.

May the risen Christ open a path of hope to all those who in other parts of the world are suffering from violence, conflict, food insecurity and the effects of climate change. May the Lord grant consolation to the victims of terrorism in all its forms. Let us pray for all those who have lost their lives and implore the repentance and conversion of the perpetrators of those crimes.

May the risen Lord assist the Haitian people, so that there can soon can be an end to the acts of violence, devastation and bloodshed in that country, and that it can advance on the path to democracy and fraternity.

May Christ grant consolation and strength to the Rohingya, beset by a grave humanitarian crisis, and open a path to reconciliation in Myanmar, torn for years now by internal conflicts, so that every logic of violence may be definitively abandoned.

May the Lord open paths of peace on the African continent, especially for the suffering peoples in Sudan and in the entire region of the Sahel, in the Horn of Africa, in the region of Kivu in the Democratic Republic of the Congo and in the province of Capo Delgado in Mozambique, and bring an end to the prolonged situation of drought which affects vast areas and provokes famine and hunger. May the Risen One make the light of his face shine upon migrants and on all those who are passing through a period of economic difficulty, and offer them consolation and hope in their moment of need. May Christ guide all persons of good will to unite themselves in solidarity, in order to address together the many challenges which loom over the poorest families in their search for a better life and happiness.

On this day when we celebrate the life given us in the resurrection of the Son, let us remember the infinite love of God for each of us: a love that overcomes every limit and every weakness. And yet how much the precious gift of life is despised! How many children cannot even be born? How many die of hunger and are deprived of essential care or are victims of abuse and violence? How many lives are made objects of trafficking for the increasing commerce in human beings?

Brothers and sisters, on the day when Christ has set us free from the slavery of death, I appeal to all who have political responsibilities to spare no efforts in combatting the scourge of human trafficking, by working tirelessly to dismantle the networks of exploitation and to bring freedom to those who are their victims. May the Lord comfort their families, above all those who anxiously await news of their loved ones, and ensure them comfort and hope.

May the light of the resurrection illumine our minds and convert our hearts, and make us aware of the value of every human life, which must be welcomed, protected and loved.

**A happy Easter to all!**




This page is Sponsored by ECC SDCO, Food Security, Resilience and WATSAN team

**"Him, being delivered by the determinate counsel and foreknowledge of God, ye have taken, and by wicked hands have crucified and slaina; Who God hath raised up, having loosed the pains of death: because it was not possible that he should be Holden of it." (Act. 2:23--24)**



# Easter Message

*of*
***His Eminence Cardinal Berhaneyesus President of Catholic Bishops' Conference of Ethiopia to all Faithful***
*May 2024*



**In The Name of The Father, and of The Son and of The Holy Spirit Amen!**

## "I am the resurrection and the life" John 11:25

*Excellency Bishops,*
*Reverend Fathers, Religious Men and Women,*
*All People of Good Will,*
*All People of God,*
*All Ethiopians and Ethiopian Diaspora Communities*

On behalf of the Ethiopian Catholic Church and myself, I offer you my best wishes of the resurrection of our Lord Jesus Christ for the year 2024. Happy Easter!

Before we explore the wonder of the resurrection of Jesus, we need to delve into the significance of his suffering on the cross. The immense pain and the glorious resurrection are deeply connected because would Jesus, the King of Glory, endure such torment? While many face hardship in pursuit of personal gain, Jesus' sacrifice wasn't driven by self-interest. His suffering wasn't a frantic scramble to fulfill a need, a path many of us find ourselves on.

The situation of Jesus is unique. He wasn't forced to suffer but driven by love and a desire for humanity's well-being, he willingly surrendered himself. The Gospels even tell us that before entering Jerusalem, while teaching in Galilee, he escaped attempts on his life (John 18:21). This highlights his power – no one could harm him without his consent. Jesus' suffering is a complex mystery, but one central truth remains: he chose to suffer and die for others.

Jesus' good works, ironically, sparked jealousy among his opponents. Blinded by this envy, they actively opposed his efforts to expand God's kingdom. Imagine someone consumed by jealousy, resorting to murder. That's the tragic parallel to Jesus' situation. His message of mercy for the ostracized and his emphasis on love as the new law didn't resonate with them. Their hearts, twisted by jealousy, bred hatred, leading to the horrific decision to crucify him. But the legacy of Jesus' suffering extends far beyond his time. It serves as a beacon of hope for all of humanity, past, present, and future. The sacrifice of Jesus, cleanses us from our sins. The first man, Adam, driven by pride, desired godliness and caused humanity's fall. In contrast, Christ, the new Adam, brought glory and resurrection through humility (Romans 5; Philippians 2).

The Resurrection is the cornerstone of our Christian faith – the ultimate good news. It shows us that death is not the end. As Saint Paul wrote in Romans 6, through baptism, we symbolically die with Christ to sin and rise with him to a new life. Christ's resurrection isn't just about human redemption; it's a promise of restoration for all creation. The world shall rejoice in a chorus of gratitude to its Creator. We, as part of this creation, share in that gratitude. Let's raise our voices in praise and celebrate the victorious Christ!

Without the resurrection, Christianity crumbles. Jesus' life on Earth would be a tragic tale, a victory for evil, and a crushing blow to humanity's hope. But the resurrection bursts forth as the ultimate triumph, defying human comprehension. Christ's death conquers death itself, vanquishes evil, and crushes Satan's grip. Despair surrenders to joy, as the true light of the world illuminates the path to life everlasting.

The resurrection revived the hope of the disciples by shattering their doubt. The beloved disciple's faith, perhaps remembering Jesus' words whispered close, led him to stand bravely by the cross. He embraced the suffering, reaching the threshold of the resurrection's profound mystery. Mary Magdalene, fearing Jesus' body had been stolen, displayed immense love and devotion in her search for him. Little did she know, she'd find far more than a corpse. Initially, she didn't recognize the risen Jesus, but when He spoke her name, a recognition echoed: "He calls his sheep by name." Mary was entrusted with a momentous task: to herald the resurrection and ascension. She was called to let go of the past, for Jesus was returning to his Father.

The Risen Christ's greeting, "Peace be with you" (Matthew 20:19), reveals a profound truth: the cross is not just about suffering, but also about peace. It reflects God's identity, offering truth about humanity and creation. This peace encompasses all that is good: the dignity of life, love, service, generosity, justice, and mercy. It even guides our work and rest. Let us celebrate the risen King! Let's honor him and spread peace in our communities, reflecting the light of his resurrection. Peace is the answer to so many problems. Let us all pray for it, and may the Lord, through his sacrifice, grant us peace and love.

Dear Sisters and Brothers in Christ,

In the spirit of Easter, let's extend this celebration to those in need. Let us come together to care for the displaced, those facing hunger, and migrants who require our support.

On this Easter Sunday, may the love and mercy of Jesus Christ embrace those who are sick and bring comfort to those who grieve. May those unjustly imprisoned be released and may those facing troubles and suffering receive strength.

Let us pray for peace in our country, Ethiopia and in the light of the resurrection, Christ our Lord Amen! May God Grant us Peace, Blessings, and Sanctification in the name of Jesus.

† Cardinal Berhaneyesus D. Souraphiel CM
Metropolitan Catholic Archbishop of Addis Abeba
President of CBCE & Chancellor of ECU

This page is sponsored by CRS

**"And if Christ be not risen, then our preaching vain, and your faith also vain." (Cor. 15:14)**

LINK

# የጥሪ ማዕድ

## የሕክምና ተልዕኮ እህቶች ማኅበር
## Medical Mission Sisters

*Called to be a healing presence at the heart of a wounded world*

**“ብርሃናችሁ በዓለም ሁሉ ይብራ”** ማቴ. 5: 16

“let your light shine” Mt. 5 - 16



ማህበራችን እ.ኤ.አ በ1925 በሲስተር አና ደንግል (ዶር) Sister Anna Dengel (Dr.) በአሜሪካ ተመሠረተ

**የማህበራችን ዋነኛው ዓላማ -** የክርስቶስን የማዳን ሥራ አገልግሎት በሕክምናና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

**መስፈርታችን -**

- በቅድሚያ ሕይወቷን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለድሆች መስጠት የምትፈልግ
- ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ ያላት
- በዓለም አቀፍ ማኅበር መኖርና ማገልገል የምትፈልግ
- የትምህርት ደረጃ 10+2 እና ከዚያም በላይ

አድራሻችን አዲስ አበባ / ቂርቆስ - ወርዳ 01
ቦሌ ጌስት ሃውስ አካባቢ
ቤት ቁጥር - 68

የስልክ ቁጥር
0911055968
0911400139
0911106561
0923241466

ፖ.ሣ. ቁጥር 2891

| | |
|---|---|
| አድራሻችን | ወልቂጤ ጉራጌ |
| ስልክ ቁጥር | 011 3 30 52 37 |
| ፖ.ሣ. ቁጥር | ሲስተር ንግሥት ብሩ 11 |

## The Services Provided by EWWCSc

- Water Wells Drilling
- Water Works Construction
- Water Works Study and Design
- Construction of Irrigation Schemes
- Spring Development
- Rehabilitation and cleaning of old water wells
- Repair and Maintenance of water works construction machinery
- Import and Distribution of machinery, rigs, water pumps, Generators, Pipes and casings including its productions
- Different water scheme constructions (pipes lying, water reservoirs, stand for water reservoirs, water points, distribution lines, sanitation and hygiene facility etc...)
- Import and Distribution of General Electro Mechanical equipment & installation (supply and installation of water pumps & generators, renewable energy sources such as solar pumps, wind pumps and water power pumps)
- Contract Administration and Bill of Quantity preparation
- Purchase and Procurement of water works machinery, equipment and construction materials
- Different Training development on water works
- Engage in rental Activity of Construction machinery and equipment
- Import and as well as production of construction materials and distributions
- Engage in Share Exchange (purchase and sell of stock)
- Engage in Production of purified water, Seal and sales

## የኮንሰላታ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች ገዳም

“የኮንሰላታ የአጽናኝቷ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች ገዳም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ያለው ሲሆን የገዳማችን ልዩ ምልክት እግዚአብሔር ኢየሱስን አጽናኝ አድርጎ ለዓለም እንደሰጠ እኛም ለዓለም ሁሉ የምሥራቹን ቃል ማብሰር ነው።”

**“.... ሕዝቤን አጽናኑ አጽናኑ” (ኢሳ. 40 :1)**

እኛ የአጽናኝቷ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች በብፁዕ ዮሴፍ አላማኖ አማካኝነት ቶሪኖ በሚባል በጣሊያን ከተማ ገዳማችን ተመሰረተ።

የተጠራነውም በፍቅር እንድንኖርና በተጠራንበት የፍቅር ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማብሰር ነው። ይህንንም የምናደርገው በሕብረት በመኖር፣ ዛሬ በምንገኝባቸው አገሮች፣ በአፍሪቃ፣ በእስያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ከማህበረሰቡ ጋር በመኖር የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**የገዳማችንን መንፈስ ለመከተልም ሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና መፅናናት ላልደረሳቸው ለማድረስ ለምትሹ እህቶች/ ወንድሞች ሁሉ -** የገዳማችን መጠይቅ እንደሚከተለው ነው

1. በቅድሚያ ራሷን/ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የምትፈልግ/ የሚፈልግ
2. የእግዚአብሔርን ቃል ላልደረሳቸው ማብሰርና የተልኮ ሕይወት ለመኖር ሙሉ ፍላጎት ያላት/ ያለው
3. 10+3 ወይም ዲፕሎማ 12+3 Degree (ዲግሪ) ከዛም በላይ በማንኛውም ዘርፍ የትምህርት ማስረጃ ያላት/ ያለው
4. ለአባቶች 12ኛ ክፍል ይቀበላሉ



Our Lady of Consolata
Pray for Us

**“ታላቅነቴን በሕዝቦች መካከል ያውጃሉ” (ኢሳ. 66 :18)**

ስልክ
**0912-14-26-37**
**011-3-21-01-47 / 48**

የፖ.ሳ ቁጥር
**145069 / 22748**

አድራሻ
**ኮንሰላታ ሲስተሮች/ አባቶች አዲስ አበባ መካኒሳ ከመካነየሱስ ሴሚናሪ ፊት ለፊት**

## በአዲስ አበባ ካቶሊክ ሃገረስብከት ሴቶች ዕድገት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማዕከል

(ካሀሴዕማ/ቴ/ሙ/ት/ስ) አ.አ.

**Catholic Archdiocese Women’s Promotion Technical and Vocational Education & Training Center**

(CAWPC / TVET) A. A

**“ Come and see us. You will be most welcome! WE ARE WAITING FOR YOU! ”**

በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙና የቀለም ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የሙያ ስልጠና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ በአነስተኛ ክፍያ የስልጠና አገልግሎት በማግኘት ለሥራ ብቁ የሚያደርጉና ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚያዘጋጁ የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**በአጫጭር ስልጠና (Short training)**
በደረጃ አንድና በደረጃ ሁለት
Level (1) one and Level (2) two

**የሚሰጡ ስልጠናዎች**

1. ልብስ ቅድና ስፌት
2. ህትመትና ማቅለም
3. የተሻሻለ የሽመና ሥራ
4. ጥልፍ በእጅና በስፌት መኪና
5. ሹራብ በእጅና በማሽን
6. ምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ

U - ከ 3-6 ወራት አጭር ኮርስና
ለ - ለ 10 ወራት በመረጡት ሙያ ሰልጥነው እራስዎን ለሥራ ያዘጋጁ።

**በማዕከአችን የስልጠና አገልግሎቱ ቀጣይነት በጥራት የሚያመርታቸውን የዕደጥበብ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጋብዛልን።**

**አድራሻችን**
አራዳ ክ/ከ ፒያሳ
ካቶሊክ ካቴደራል ት/ቤት
ቅጥር ግቢ ውስጥ

**ስልክ ቁጥር**
011 111 4786 / 011 157 5927

**E-mail**
cawpc@ethionet.et

**ወንጌልን በጋራ እንስበክ**

**ሌሎች ቢያነቡዋቸው ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለው የሚያምኑባቸውን መጣጥፎች እና የወንጌል አስተምህሮዎች ይላኩልን**

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org